በኢትዮጵያፌዴራላዊዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡
የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2009 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ /የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

የወጪ ሂሳብ፣

1. ሚ/ር መ/ቤቱ የጉልበት ሰራተኛ በሚል በቋሚ ሠራተኞች የሚሠሩ የንብረት ክፍል ማደራጀትና የመላላክ ሥራ እንዲሠሩ ቅጥር ፈጽሞ ብር 42,300.00 ተከፍሎ መገኘቱ፣
2. በብር 2,001,752.59 ለኮምፒውተር ግዥ ከካፒታል በጀት የተገዛና ከተጠቃሚዎች የግዥ መጠየቂያ ሳይቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ ከዚህ ከተጠቀሰው ገንዘብ ውስጥ አለአግባብ ባልተደለደለ በጀት ከግል ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት የሂሳብ መደብ 6251 (በውል የሚፈጸሙ የሙያ አገልግሎቶች) ከሚለው ብር 463,632.39 ግዥ ተፈጽሞ መገኘቱ፣

3. ማንኛውም የአገልግሎት ግዥዎች በግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም ሲገባው አለአግባብ ደንብና መመሪያ ውጭ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-

   - ለደሳለኝ ሆቴል ብር 146,107.51 መክፈል ሲገባው፣ ብር 183,090.50 በመክፈሉ በብልጫ ብር 36,982.99 ተከፍሎ መገኘቱ፣
   - ለመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ብር 111,413.29 መክፈል ሲገባው፣ ብር 135,858.39 በመክፈሉ በብልጫ ብር 24,445.10 ተከፍሎ መገኘቱ፣

   በድምሩ ብር 61,428.09 በብልጫ ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱን፣

4. የማስታወቂያ ሥራ ለመሠራቱ፣ ውድድር ለመደረጉ እና የሥራ ውል ማስረጃ ሳይቀርብ፣ ለሲስኮም ኃ/የተ/የግ/ማህበር የማስታወቂያ ስራ ክፍያ በሚል ብር 20,470.00 ከሂሳብ መደብ 6251 (በውል የማማከር ስራ) ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
5. ማንኛውም የአገልግሎት እና የዕቃ ግዥዎች በግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም ሲገባቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-
   - በብር 7,813,754.98 ያለምንም ውድድር የጥበቃ፣ የመስተንግዶ፣ የእድሳት፣ የሥልጠና፣ የማማከር እና አንቲ ቫይረስ ግዥ በቀጥታ ግዥ መፈፀሙን፣
   - በብር 844,251.15 የተለያዩ ግዥዎች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ መፈፀም የሚገባውን የመስተንግዶ፣ የሥለጠና፣ ለትራንስፖርት እና ቴሌቪዥን ገዥዎች በቀጥታ ግዥ መፈፀሙን፣
   - በብር 991,060.19 የኮምምፑዩተር ግዥ በጥቅል በጨረታ ሂደት መገዛት ሲገባው፤ በአንድ ቀን ከተለያዩ ድርጅቶች በመቆራረጥ በዋጋ ማወዳደሪያ የተገዛ እና የተጠየቀው 200 ሲሆን የተገዛው ግን ብዛት 597 ከመጠየቂያው በ397 የሚበልጥ መገዛቱን፣
6. በድምሩ ብር 3,258,398.86 በስልጠና እና በስብሰባ መስተንግዶ የተሳታፊዎች ዝርዝር ስለመሳተፋቸው፣ የሰዓት መቆጣጠሪያ ማስረጃና እነማን እንደተሳተፉ ማስረጃ ባልቀረበበት ክፍያዎች ተፈፅመው መገኘቱ፣
7. በብር 1,243,936.00 ባልተፈቀደ በጀት ለድጋፍ (ስፖንሰር) የተከፈለና ያለሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ መገኘቱን፣
8. በተለያየ የሂሳብ መደብ ብር 12,789,120.84 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡

9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመደበኛ ስራ ለመስተንግዶ ወጪ ብር 2,418,153.79 ከካፒታል በጀት ባልተፈቀደ የሂሳብ መደብ መጠቀሙን፣

10. ብር 245,000,00 ከመደበኛው በጀት ለቦንድ ሽልማት በማለት የተዘረጋ እና የተፈቀደ ሥርአት ሳይኖር ያለደንብና መመሪያ ለሽልማት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣

11. የጨረታ ሂደት ተከትሎ ያልተፈጸመ ግዥ፣-

- ለConsultancy services for development of Ethiopian national E-commerce platform ለተሸጠው የግዥ ጨረታ ሰነድ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-
  - ሌሎች ተጫራቾች እያሉ በጨረታ ያልተሳተፈ እና የጨረታ ሰነድ ያልገዛ Grail consulting Service Pvt.Ltd የተባለ ድርጅት እንደተሳታፊ አድረጎ ማቅረቡን፣
  - አሸናፊ ያልሆነ ድርጅት ማለትም Grail consulting Service Pvt.Ltd በብር 5,714,521.05 Letterr of Credit እንዲከፍት ማድረጉን፣
  - የፓርትነር ማስረጃ ሳይቀርብ ከPERAGO INFORMATION SYSTEMS PLC ከተባለው ድርጅት ፓርትነር ናቸው በማለት ብር 1,459,124.02 የተከፈለ መሆኑን፣
  - እንዲሁም ድርጅቶቹ የባንክ ጋራንቲ እና ሲፒኦ በወቅቱ ስለማቅረባቸው ማስረጃ ያልተያያዘ መሆኑን፣

  በድምሩ ብር 7,173,645.07 የግዥ ሂደቱን ሳይከተል ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ Consultancy services for development of Online content Regulation framework for Ethiopia ለወጣው ጨረታ የመነሻ ገንዘቡ ሳይታወቅ አሸናፊ ተብሎ የተገለጸዉ ድርጅት PERAGO INFORMATION SYSTEMS PLC እያለ መነሻ ገንዘቡ ላልታወቀ ድርጅት ከድርጅቱ ጋር ሲወዳደር ለነበረዉ ለLeading Assocciation ብር 931,930.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን እና በተጨማሪም የፓርትነር ማረጋጋጫ ሳየይቀርብ Leading Assocciation ከ Grail consulting Service Pvt.Ltd ጋር ፓርትነር ናቸው በማለት ለGrail consulting Service Pvt.Ltd ደግሞ ብር 3,036,770.94 (በዶላር 116,000.00 USD) Letterr of Credit ለመክፈት ወደ ባንክ ተቀማጭ መደረጉን፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ Development of online Customer Compliant and Suggestion Management System ለወጣው ጨረታ የቴክኒክ ግምገማውን የሚያሟላው ብቸኛ አሸናፊ በሚል PERAGO INFORMATION SYSTEMS PLC በብር 3,489,675.00 ውል የፈጸመ ሲሆን፣ ከድርጅቱ ጋር የቴክኒክ ውድድር ያደረገው Custor Computing PLC ምን ያህል ዋጋ እንዳቀረበ ሳይታይ የፋይናንሻል ኦዲት ሪፖርት ያላቀረበ መሆኑን በቴክኒክ ግምገማው በመጥቀስ ካለምንም የዋጋ ማነፃፀሪያ እና የገበያ ዋጋ ጥናት ማስረጃ ባልቀረበበት ግዥ መካሔዱ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ Development of electronic public procurement system በቴክኒክ ግምገማ ያለፉት ድርጅቶች በፋይናንሻል ሲወዳደሩ CSM/Africom Technologies ያቀረበው ብር 3,477,600.00 ሲሆን፣ PERAGO INFORMATION SYSTEMS PLC ያቀረበው ደግሞ ብር 3,501,922.50 በመሆኑ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 8፥ሀ መሰረት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው CSM/Africom Technologies ማለፍ ሲገባው PERAGO INFORMATION SYSTEMS PLC እንዲያልፍ መደረጉ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ Content Management System with SOA Training የግልፅ ጨረታ ወጥቶ በውድድሩ በብር 386,400.00 ያሸነፈው Sysmbol Technologies የአሰልጣኝ ለውጥ በማድረጉ መ/ቤቱ ያልተቀበለው ሲሆን፣ ሁለተኛ ዝቅተኛ ያቀረበው E-System Africa ብር 661,250.00 መመረጥ ሲገባው፣ ለITSC PLC በብር 744,625.00 እንዲመረጥ መደረጉና የተፈለገው አሰልጣኝ ስለማሟላቱ ሳይረጋገጥ እንዲሠራ መደረጉ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ Support and Maintenance of Government Portals and 129 Information eService's ግልፅ ጨረታ እንዳወጣና ብቸኛ ተወዳዳሪ እንደሆነ በመግለፅ ከE-Systems Africa ላቀረበው ዋጋ ብር 7,015,000.00 ከገበያ ጋር ስለመቀራረቡ ዋጋ ሳይጠና ከተያዘው በጀት ብር 6,900,000.00 ጋር በማነፃፀር ውል የተገባ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ላልተወዳደረውና ውል ላልገባው ለግስላ ጀነራል ቢዝነስ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ድርጅት በበጀት ዓመቱ ከታየው ውስጥ ብር 2,860,941.25 የተከፈለ መሆኑ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዳታ ማዕከሉ ጥገና እንዲከናወን በቀረበው ፍላጎት ግልፅ ጨረታ ለማውጣት ጊዜ ስለሚወስድ በማለት በውስን ጨረታ ድርጅቶችን በመጋበዝ ከሳሙኤል አሰፋ የሕንፃ ሥራ ተቋራጭ ብር 5,926,525.00 የጥገና ግዥ የተፈፀመ መሆኑ፣ በተጨማሪም በተለያዩ ወረዳዎች የሚገኙ የኮሙኒቲ ሬዲዮኖች በጊዜው ተወዳድሮ ስራውን ያሸነፈው ድርጅትየሳውንድ ፕሩፍ እና የፊኒሽንግ ስራዎችን ሳያጠናቅቅ ጥሎ በመሄዱ በማለት ስራውን ለመጨረስ በቀጥታ ግዥ ብር 5,692,500.02 ለዚሁ ድርጅት የተሰጠ መሆኑን፣
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የማከራየት ፍቃድ ካለው ድርጅት የመኪና ኪራይ አገልግሎት ግዥ መፈፀም ሲገባው የህዝብ ማመላለሻ የግል ትራንስፖርት ማህበር ፍቃድ ካለው ድርጅት ጋር የትራንስፖር ኪራይ ላቀረበበት በማለት የግዥ ሂደቱን ያልተከተለና የንግድ ፍቃድ ለሌለው ብር 1,598,780.00 የተከፈለ መሆኑን፣

<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

12. በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በድምሩ ብር 212,154,657.39 የተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ ሲሆን፣ የዝርዝር መነሻ ቋት ድምር ብር 210,936,066.58 በመሆኑ ከመነሻ ሂሳብ ሰነዱ ጋር ሲገናዘብ በብር 1,218,590.81 ሪፖርቱ በመብለጥ የሚታይ መሆኑን፡-
13. ብር 64,094.00 ከለቀቁ ሠራተኞች ያልተሰበሰበ መሆኑን፣

<u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

14. በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በድምሩ ብር 53,945,245.34 የተከፋይ ሂሳብ የሚታይ ሲሆን፣ የዝርዝር መነሻ ቋት ድምር ብር 53,988,399.20 በመሆኑ ከመነሻ ሂሳብ ሰነዱ ጋር ሲገናዘብ በብር 43,153.86 የዝርዝር መነሻ ቋት በመብለጥ የሚታይ መሆኑን፣
15. ብር 133,297.16 በሂሳብ መደብ 5058 (የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ) የተመዘገበ ሲሆን ገንዘቡ በዕዳነት የተያዘበት/የተመዘገበበት ቀን፣ ወርና ዓ.ም የሌለውና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባለበጀት መ/ቤት ሆኖ ሳለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ መታየቱ፣

<u>በጀት፣</u>

16. በ2009 በጀት ዓመት በሂሳብ መደብ 6116 (ለሰራተኞች የሚደረጉ የተለያዩ ክፍያዎች) ብር 299,280.39 ባልታወጀ በጀት ዝውውር በማድረግ በወጪ ተይዞ መገኘቱ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 16 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፤ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለጥበቃ እና ለፅዳት ቋሚ ሠራተኞች እንዳሉትና አገልግሎት እየሰጡ ለመሆኑ እየታወቀ፣ ከዚህ በተጨማሪ ከሴፍ የጥበቃ አገልግሎት ከተባለ ድርጅት ለውጭ ደንበኛ (Out Sources) በማድረግና በመዋዋል የጥበቃ እና ፅዳት አገልግሎት የሰጠበትን ብር 1,067,120.16 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣

ሌሎችጉዳዮች፣

ንብረት፣

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የንብረት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች ያሉበት መሆኑ፣
- በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተጠቀሙት የነዳጅ መጠንና ከሽፈኑት የኪ/ሜትር ርቀት በየጊዜው ምዝገባ ጋር የማስታረቅ ስራ አለመሠራቱ፣

ልዩ ልዩ፣

- የጣት አሻራ የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት እንደማይቆጣጠረውና በየጊዜው ሲስተሙን የማስተካከል (Up Date) እንደማይደረግ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የሚኒስቴሩን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የሚኒስቴሩን የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሣብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴሩ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

1.1.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ከመዋቅር ውጭ የተከፈለ የጥበቃና የፅዳት አገልግሎት፣</u>

የፌዴራል መንግሥት ሠራተኛች አዋጅ ቁጥር 515 አንቀጽ 4 ስለመስሪያ ቤቶች አደረጃጀት ንዑስ አንቀጽ 1 "ማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤት የተቋቋመበትን ዓላማ ስኬታማ ለማድረግ የሚያስፈልገውን አደረጃጀትና የሰው ሀይል ፍልጎት አጥንቶ ይወስናል፡፡" በሚለው መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያለው የሰው ሀይል ባጠናው መዋቅር መሰረት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በመዋቅር የተፈቀደው ለጥበቃ 13 እና ለፅዳት 21 ቋሚ ሰራተኛ እንዳለውና አገልግሎት እየሰጡ ለመሆኑ የሰው ሀይል ሰነድ ያስረዳል፡፡ ይሁንና ከዚህ በተጨማሪ ከሴፍ የጥበቃ አገልግሎት ከተባለ ድርጅት ለውጭ ደንበኛ (Out Sources) በማድረግና በመዋዋል የጥበቃ እና ፅዳት አገልግሎት የሰጠበትን ብር 1,067,120.16 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

1.1.2 <u>ስጋት፣</u>

ላልተፈቀደ እርከን ውስን የመንግስት ገንዘብ ያላግባብ እንዲወጣ በር ሊከፍት ይችላል፡፡

1.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአይቲ ፓርክ ኮርፖሬሽን እንጂ ለሜክሲኮና ሌላም ቦታ ላሉ ቢሮዎች ከተፈቀደው ቋሚ የጥበቃና የፅዳት ሠራተኞች የሥራ መደብና ብዛት ጋር የሚገናኝ እንዳልሆነ የተገለፀ ቢሆንም ውሉን ለማየት እንደተቻለው፣
- የውል ቁጥር 555/133/09 በቀን 22/02/09 ልደታ ክፍለ ከተማ ለሜክሲኮ የሚገኘውን የሚኒስቴሩ ዋና መስሪያ ቤት ንብረቱን፣የሰራተኞቹንና የደንበኞችን ደህንነት ለማስጠበቅ ቅዳሜና እሁድ ጨምሮ 24 ሰዓት አገልግሎት፣
- የውል ቁጥር 555/134/09 በቀን 22/02/09 ኦሮሚያ ክልል ፊንፌኔ ዙሪያ አሸዋ ሜዳ ንብረቱን፣የሰራተኞቹንና የደንበኞችን ደህንነት ለማስጠበቅ ቅዳሜና እሁድ ጨምሮ 24 ሰዓት አገልግሎት፣

የውል ቁጥር 555/810/08 በቀን 16/12/08 ልደታ ክፍለ ከተማ የቀድሞ ፓፓሲኖስ ህንፃ የሚገኘውን የሚኒስቴሩ መስሪያ ቤት መጋዘን ንብረቱን፣የሰራተኞቹንና የደንበኞችን

ደህንነት ለማስጠበቅ ቅዳሜና እሁድ ጨምሮ 24 ሰዓት አገልግሎት ለውጭ ደንበኛ (Out Sources) መደረጉን ከውሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ የተሰጠው መልስ ትክክል አይደለም፡፡

1.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

በርግጥ በመዋቅር የተፈቀዱት የጥበቃና የጽዳት መደቦች ሜክሲኮና በአቅራቢያው ለሚገኙ ቢሮዎች አገልግሎት ነው፡፡ የአይቲ ፓርክ ኮርፖሬሽን ደግሞ ከአዲስ አበባ ከተማ በስተምስራቅ በቦሌ ለሚ አካባቢ የሚገኝ እና በ200 ሄክታር የቆዳ ስፋት ላይ ያረፈ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ አውላላ ሜዳ ላይ የሰፈረው የአይሲቲ መንደር አስተማማኝ አጥር የሌለው፣በውስጣቸው በርካታ ንብረቶች የሚገኙባቸው ትላልቅ ህንጻዎች የሚገኙበት፣ ከፍተኛ ዋጋ የወጣበት መሰረተ-ልማት ያለው በመሆኑ ለአደጋ የተጋለጠ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ይህ ከፍተኛ ወጪ የወጣበት የሀገር ሀብት ለአደጋ መጋለጥ ስለሌለበት የጥበቃ እና የጽዳት አገልግሎት OUT SOURCE ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የመዋቅርና የአደረጃጀት ጥያቄዎች በፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር እንዲቆሙ በመደረጉ ነው፡፡ እገዳው ሲነሳ ግን ፓርኩ በአስፈላጊው አደረጃጀት እንዲጠናከር ስለሚደረግ ሌሎች መደቦችን ጨምሮ የጥበቃ እና የጽዳት አገልግሎትም እንዲፈቀድ ይደረጋል፡፡ እስከዚያው ግን ባለው ሁኔታ መቀጠሉ የግድ እንደሚል ግንዛቤ ሊጨበጥበት ይገባል፡፡

1.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምላሽ ሲሰጥ የአይቲ ፓርክ ኮርፖሬሽን ባለው እርቀት እና ስፋት ከፍተኛ የሆነ ንብረት ስላለበት እና ካለበት ቦታ እርቀት ጋር ያውን ችግር ቢያነሳም ከሰነዱ እንደ ተረዳነው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እያስጠበቀ ያለው ሜክሲኮ የሚገኘውን የሚኒስቴሩ ዋና መስሪያ ቤት (አልታ እና ጨለለቅ ህንፃ)፣ አሸዋ ሜዳ ለሚገኘው መጋዘን እንዲሁም የቀድሞ ፓፓሲኖስ ህንፃ ፖስታ ቤት የሚገኘውን መጋዘንም መሆኑን ከውሉ እና ከክፍያ ሰነዱ ማረጋገጥ ስለሚቻል የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የእርምትና የማስተካከል ስራ መስራት ይኖርበታል፡፡ መልስም ሲሰጥ ትክክለኛ መልስ መመለስ አለበት፡፡

1.2.1 <u>ግኝት፣ የቀን ወይም ኮንትራት ሠራተኛ ሳይፈቀድ የተቀጠሩ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515 አንቀጽ 4 "ጊዜያዊ ሠራተኛ" ማለት በመንግስት መሥሪያ ቤት ውስጥ የዘላቂነት ባህሪ በሌለው ስራ ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የስራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ነው፡፡ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም ንዑስ አንቀፅ ሀ-መ ይላል፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህ መሰረት ስለመስራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከሰው ኃይል አስተዳደር በመዋቅር የተፈቀደው 367 ሲሆን አሁን ያለው የሰው ሀይል 301 መሆኑን እና የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ ኢትዮ አይሲቲ ቪሌጅ የኮንትራት ሰራተኛ 16 መሆናቸው የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክትሬት የሰጠን መረጃ ያሳያል፡፡ ይሁንና ሚ/ር መ/ቤቱ የጉልበት ሥራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የቀን ሠራተኞችን ማሠራት ሲገባ፣ ዳይሬክቶሬቱ በቁጥር ሠ/4298/09 በቀን 30/11/08 የጉልበት ሰራተኛ በሚል በማስታወቂያ ቦርድ ላይ በማውጣት የንብረት ክፍል ማደራጀትና የመላላክ ሥራ እንዲሠሩ ቅጥር ፈጽሞ ብር 42,300.00 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

1.2.2 <u>ስጋት፣</u>

ባለው ክፍት የስራ መደብ ሰራተኛ አወዳድሮ እንዳይቀጥር ሊያደርገው እና የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣው ደንብና መመሪያ ተግባራዊ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህም የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

1.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ እያሰራ ያለው የመደበኛ ስራ እንጂ የቀን ሰራተኛ የሚሰራውን ስራ ባለመሆኑ ባለው ክፍት የስራ መደብ ባላቸው የትምህርትና የስራ ልምድ ጋር አጣምሮ ባሉት ቦታ መቅጠርና ማሳደግ ሲገባው ለበርካታ ወራት በጊዜያዊነት መዋቅጠሩ በመንግስት ስራ ላይ ተፅእኖ ከማስከተሉም ውጭ የውስጥ ቁጥጥር ስራዓቱ ድክመት የሚያሳይ በመሆኑ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጀት የሚፈቀድለት በዕቅድ ለተያዙ ሥራዎች መሆኑን አውቆና ተገንዝቦ በበጀት መደብ ላልተካተተ ወጪ ክፍያ መፈጸም አይኖርበትም፡፡

1.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ዳይሬክቶሬቱ በቀን 30/11/08 የጉልበት ሰራተኛ በሚል በማስታወቂያ ቦርድ በማውጣት የንብረት ክፍልን የማደራጀትና የመላላክ ስራ እንዲሰሩ ቅጥር ፈጽሟል፣ስለሆነም ባለው ክፍት የስራ መደብ ሰራተኞቹን መቅጠርና ማሳደግ ሲገባው ለበርካታ ወራት በጊዜያዊነት መቅጠሩ ትክክል አይደለም በማለት የኦዲት ግኝት ቀርቧል፡፡ በመሰረቱ የቀን ተከፋይ የሆኑ የቀን ሰራተኞችን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለው ክፍት የስራ መደቦች ላይ መቅጠርና ማሳደግ ፈጽሞ አይችልም፡፡ የቀን ሰራተኞቹ በቋሚነት መቀጠር ካለባቸው ክፍት የስራ መደቦቹ የሚጠይቁትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነና እንደማንኛዉም ተወዳዳሪ ክፍት መደቦቹን ለመሙላት በጋዜጣ ማስታወቂያ ከወጣ በኋላ መመዝገብና መወዳደር ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ በሰው ኃይል መራጭ ኮሚቴ ከተመረጡ ወደ ስራው ይቀላቀላሉ እንጂ በቀን ሰራተኛነት የተቀጠሩትን ወደ መደበኛ ቅጥር የማሸጋገርም ሆነ በደረጃ እድገት የማሳደግ አካሄድ ከአሰራርና ከመመሪያ ውጭ ነው፡፡ ስለዚህ ለወደፊቱም ቢሆን የቀን ስራ በሚጠይቁ ስራዎች ላይ የቀን ተከፋይ ሰራተኞችን ማሰራት ሊኖር ስለሚችል በዚህ መልኩ መረዳት ይገባል፡፡

1.2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም "የቀን ተከፋይ የሆኑ የቀን ሰራተኞች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለው ክፍት የስራ መደቦች ላይ መቅጠርና ማሳደግ ፈጽሞ አይችልም፡፡" ቢልም በማስታወቂያ ቦርድ ላይ ወጥቶ ቅጥሩ የተፈፀመና ክፍያውም በየወሩ እየተከፈለ ያለ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡የቀን ተከፋይ ማለት ለዕለቱ ለሰሩበት የጉልበት ስራ በግዜው የሚከፈል ሲሆን ለተከታታይ ወር ክፍያ መከፈሉና በቋሚ ሰራተኛ ሊሰራ የሚችለውን ስራ እየሰሩ እያለ የጉልበት ሰራተኛ መባሉ የተሰጠው ምላሽ ትክክል አይደለም፡፡ በመሆኑም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጠውን አስተያየት ተቀብሎ የእርምት እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

1.3.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ከግዥ መጠየቂያ ውጭ፣ ከሚከፈለው በላይና ያለማስረጃ የተከፈለ፣</u>

የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) "ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ አለበት፡፡" ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፡-

- በቀን 08/04/09 ዓ/ም በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 733960 በሂሳብ መደብ 6251 እና 6313 በወጪ የተያዘ ብር 2,001,752.59 ለኮምፒውተር ግዥ ከካፒታል በጀት የተገዛና ከግል ዘርፍ ዳይሬክቶሬት፣ ከኤ-መንግስት ዳይሬክቶሬት እና ከኢትዮ-አይሲቲ ቪሌጅ ዳይሬክቶሬት የግዥ መጠየቂያ ሳይቀርብ፤ ባልተደለደለ በጀት ከግል ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት የሂሳብ መደብ 6251 (በውል የሚፈጸሙ የሙያ አገልግሎቶች) ከሚለው ብር 463,632.39 ግዥ መካሄዱ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አገልግሎቱን በደሳለኝ ሆቴል የተጠቀመው ከቀን 25-27/05/2009 የባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 330292 ብር 183,090.50 የተከፈለ ሲሆን፣ መከፈል የነበረበት ብር 146,107.51 መሆን ሲገባው፣ በአንድ ቀን ሁለት ደረሰኝ በመቆረጡ ምክንያት ብር 36,982.99 በመብለጥ ተከፍሎ መገኘቱ፡-
- ለመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን በ10/02/09 የባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 733807 ብር 135,858.39 የተከፈለ ሲሆን፣ መከፈል የነበረበት ብር 111,413.29 መሆን ሲገባው፣ በአንድ ቀን በሁለት ደረሰኝ በመቆረጡ ምክንያት ብር 24,445.10 በመብለጥ ተከፍሎ መገኘቱ፡-
- የማስራወቂያ ሥራ ለመሠራቱ፣ ውድድር ለመደረጉ እና የሥራ ውል ማስረጃ ሳይቀርብ፣ በባንክ ማስመስከሪያ ቁጥር 330100 በ28/09/09 ለሲስኮም ኃ/የተ/የግ/ማህበር የማስታወቂያ ስራ ክፍያ በሚል ብር 20,470.00 ከሂሳብ መደብ 6251 (በውል የማማከር ስራ) ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣

የግዥ መጠየቂያ ሳይቀርብና የተደለደለ በጀት ሳይኖረው ብር 2,001,752.59፣ ከተጠየቀው በላይና በብልጫ ብር 61,428.09 ተከፍሎ የተገኘ እና ማስረጃ ሳይኖረው ብር 20,470.00 የተከፈለ በድምሩ ብር 2,162,118.04 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

1.3.2 <u>ስጋት</u>፣

የሆቴል ግዥ ሂደቱን አጠራጣሪ ሊያደርገው፣ያልተጠየቁ ንብረቶች በብዛት ተገዝተው በስቶር ውስጥ ሊመቀጡ እና ንብረቶ ች ለብክነት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

1.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከግል ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት የሂሳብ መደብ 6251 (በውል የሚፈጸሙ የሙያ አገልግሎቶች) ከሚለው ብር 463,632.39 ግዥ መካሄዱ፣ ባልተፈቀደ

በጀት ግዥ መፈፀም ለታለማለት አላማ እንዳይወጣ ያደርገዋል ግዥም ሳይጠየቅ መገዛቱ ብክነትን ያሳያል፡፡ ከተደለደለው በጀት ውጭ የተገዛውም አግባብነት የለውም፡፡

- ለከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ለሌሎች ተሳታፊዎች የማስተናገጃ ቦታው ማለትም ለVIP የዋጋ ልዩነት ሳይኖረው በቦታዎች መለያየት አስተናጋጆች የየራሳቸውን በማስቆረጣቸው የተፈጠረ እንጂ በብልጫ የተከፈለ በማለት በኦዲት ወቅት የተሰጠው ምላሽ ትክክለኛ መልስ አይደለም፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱ ጠንካራ እንዲሆን መስራት ይጠበቅበታል፡፡ በብልጫ ተከፍሎ የተገኘውም ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.3.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- በ8/4/09 በባንክ ማስመስከሪያ ቁጥር 733960 ለኮምፒውተር ግዥ ከካፒታል በጀት ተገዛ ለተባለው ሚ/ር መ/ቤቱ ከሚያከናውናቸው ዋና ሥራዎች አንዱ በኢ-መንግሥት ዳይሬክቶሬት በኩል የሚፈጸም ለማኅበረሰብ አገልግሎት ለተደራጁ በኤሌክትሮኒክስና ተዛማጅ ዕቃዎች በማቅረብ ድጋፍ መስጠት ሰለመሆኑ ለዚሁ የሚውል በካፒታል በጀት ተፈቅዶ የተገዛ እንጂ የመደበኛ ወጪ ባለመሆኑ መሆኑ ግንዛቤ እንደያዝልን፡
- በባንክ ማስመስከሪያ ቁጥር 330292 እና በ733807 የተጠቀሰውን አስመልክቶ በአንድ ቀን ሁለት ደረሰኝ በመቆረጡ ምክንያት በብልጫ የተከፈለ ገንዘብ እንዳለ ተጠቅሶ የተገለጸውን አስመልክቶ ይህ የሆነበት ምክንያት በሆቴሉ ማስተናገጃ ቦታዎች ለከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ለሌሎች ተሳታፊዎች የማስተናገጃ ቦታው ማለትም ለVIP የዋጋ ልዩነት ሳይኖረው በቦታዎች መለያየት አስተናጋጆች የየራሳቸውን በማስቆረጣቸው የተፈጠረ እንጂ በብልጫ የተከፈለ ያለመሆኑ ግንዛቤ እንዲያዝልን እንጠይቃለን፡፡

1.4.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>በጨረታ ዘዴ ግዥን መፈፀም ሲገባ በቀጥታ የተገዛ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 33 የግዥ ዘዴዎች ንዑስ አንቀጽ 2 "የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፡፡"ንዑስ አንቀጽ-3 "የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በዚህ አዋጅ የተገለፁት ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ይሆናል፡፡" ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ሚ/ር መ/ቤቱ ያለምንም ውድድር በብር 7,813,754.98 በቀጥታ ግዥ መፈፀሙን ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡-

ተ.ቁ	አቅራቢ ድርጅት ስም	የደረሰኝ ቁጥር	ቀን	የተገዛው ግዥ	የገንዘብ መጠን
1	ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል	BPV-733706	30/08/09	መስተንግዶ አገልግሎት	1,192,895.00
2	በርመኮን ኢንጅነሪግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር	BPV-733776	25/01/09	እስቶር እድሳት	2,964,999.57
3	ኤክሲድ አይቲ ሲስተምስ ኃ.የተ.የግ.ማህበር /ኤ-መንግስት/	BPV-733751	12/01/09	የማከር ስራ	96,600.00
		BPV-733649	27/11/08	ካስተርሲኪ አንቲቫይረስ	371,450.00
4	ዲጂታል አይ.ቲ.ኮንሰልቲንግ-/ኢትዮ ኤሲቲ ቪሌጅ/ One-Stop Service Delivery.	BPV-733665	06/12/08	የሙያ ማማከር ግዥ	579,858.75
		BPV-733743	10/01/09		386,751.50
5	አህዱ ቴክ አይሲቲ ሶሊሽን ኃ.የተ.የግ.ማህበር. /ኢ-መንግስት/	BPV-733871	05/03/09		105,800.00
		BPV-733963	08/04/09		428,572.50
6	ኢንፎሳይስ ኃ.የተ.የግ.ማህበር-/Cash Registration Machine Recite not attached. / /ኢትዮ ኤሲቲ ቪሌጅ/	BPV-733752	12/01/09		414,000.00
		BPV-733908	03/12/09		276,000.00
7	ሴፍ የጥበቃ አገልግሎት ኃ.የተ.የግ.ማህበር	BPV-733757	16/01/09	የጥበቃ አገልግሎት	192,747.66
		BPV-733790	02/02/09		191,360.00
		BPV-733869	02/03/09		191,360.00
		BPV-733977	16/04/09		210,680.00
		BPV-330156	24/05/09		24,150.00
		BPV-330166	29/05/09		186,530.00
ጠቅላላ ድምር ብር					7,813,754.98

1.4.2 ስጋት፣

በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ በግዥ አፈፃፀም ረገድ የመንግስት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ላያስገኝ ይችላል፡፡ ይህም ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣

ቁጠባን የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ያላስፈልጊ ወጪ ሊሆን ይችላል፡፡

1.4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ግዥ የተከናወነው በበላይ ኃላፊ ትዕዛዝ፣ አዋጅና መመሪያ መሰረት ተከትሎ፣ የውስን ጨረታ ግዥ ሂደት ተከትሎ እና የጥበቃ አገልግሎት እንደሚያስፈልግ ታምኖበት መሆኑን ቢገልፅም የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም በበላይ ኃላፊ የሚፈቀዱት በዕቅድ ላልተያዙ እና አስቸኳይ ሲያጋጥም እንጂ ቀድሞ ለታቀደ በየ6 ወሩ ለሚደረግ ስብሰባ ቀጥታ ግዥ መፈቀዱ ህጉን የሚጋፋ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ሌሎችም መልሶች እንደተባለው አዋጅና መመሪያ መሰረት ተከትሎ ቢሆን ኖሩ እንደ ግኝት አይጠየቅም ነበር፡፡ ውስን ጨረታ መካሔድ ያለበት ቀድሞ ሌሎች የግዥ ሂደትን ከታለፈ ሲሆን ቀጥታ ወደ ውስን ጨረታ መግባት የማይቻልና ግዥውም ቢሆን የውስን ጨረታ ሂደትን ተከትሎ ያልተገዛ መሆኑን ከሰነዱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የግዥ ሂደቱን በማጤንና በመገንዘብ ለወደፊቱ በህጉ ብቻ መሰራት አለበት፡፡

1.4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

1- <u>ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል፡</u>

በየአመቱ በሚደረገው ለመ/ቤቱ ሰራተኞች ስልጠናዊ ግምገማ ማካሄጃ የሆቴል ኪራይ እና የምግብ ወጪ በበላይ ኃላፊ ትዕዛዝ ግዥው ተፈቅዶ ስራው የተከናወነ መሆኑንና ለዚህም ፈቃድ ከክፍያው ማስረጃው ጋር ተያይዞ የሚገኝ መሆኑን፡፡

2- <u>በርመከን ኢንጅነሪንግ ኃ.የተ.የግ.ማ</u>

በአዋጁና በመመሪያው መሰረት የውስን ጨረታ ግዥ ሂደት ተከትሎ ግዥ የተከናወነ

3- <u>ኤክሲድ አይቲ ሲስተምስ ኃ.የተ.የግ ማህር</u>

1. በሄራልድ ጋዜጣ October 20/2015 በወጣው ጋዜጣ ላይ ግልፅ ጨረታ እንደታወጀ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡
2. 14 ተወዳዳሪዎች ሰነዱን ገዝተዋል፡፡
3. ጨረታውን የተሳተፉት 5 ተወዳዳሪ ድርጅቶች ተሳትፈዋል፡፡

4. በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ተከትሎ ግዥው የተፈፀመ፡፡

4- <u>ዲጂፋይ አይቲ ኮንሰልቲንግ /ኢትዮ አይሲ ቲ ቪሌጅ</u>

1. በሄራልድ ጋዜጣ መስከረም 20/2015 በወጣው ጋዜጣ ላይ ግልፅ ጨረታ እንደታወጀ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡
2. 5 ተወዳዳሪዎች ሰነዱን ገዝተዋል፡፡
3. ጨረታውን የተሳተፉት 3 ተወዳዳሪ ድርጅቶች ተሳትፈዋል፡፡
4. በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ተከትሎ ግዥው የተፈፀመ፡፡

5- <u>አሃዱቴክ አይሲቲ ሶሉሽን ኃ.የተ.የግ.ማህበር</u>

1. በሄራልድ ጋዜጣ November 15/2014 በወጣው ጋዜጣ ላይ ግልፅ ጨረታ እንደታወጀ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡
2. 28 ተወዳዳሪዎች ሰነዱን ገዝተዋል፡፡
3. ጨረታውን የተሳተፉት 5 ተወዳዳሪ ድርጅቶች ተሳትፈዋል፡፡
4. በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ተከትሎ ግዥው የተፈፀመ፡፡

6- <u>ኢንፎሲስ ኃ.የተ.የግ.ማህበር</u>

1- በሄራልድ ጋዜጣ December 03/2016 በወጣው ጋዜጣ ላይ ግልፅ ጨረታ እንደታወጀ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡

2- 3 ተወዳዳሪዎች ሰነዱን ገዝተዋል፡፡

3- ጨረታውን የተሳተፉት 2 ተወዳዳሪ ድርጅቶች ተሳትፈዋል፡፡

4- በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ተከትሎ ግዥው የተፈፀመ፡፡

7- <u>ሴፍ የጥበቃ አገልግሎት ኃ.የተ.የግ.ማህበር</u>

እንደሚታወቀው አይቲ ፓርክ በመ/ቤቱ ስር ሆኖ እንደሚተዳደር ይታወቃል፡፡ ቀደም ብሎ ህንፃው ሲጀመር እና አሁን ላለው ንብረት የጥበቃ አገልግሎት እንደሚያስፈልግ ታምኖበት በዚህ መሰረት የጥበቃ አገልግሎቱ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

1.4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውንም ግዥ ሲፈፅም በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ መሰረት በተገለጹት የግዥ ዘዴዎች መሠረት በውድድር መሆን አለበት፡፡ ለወደፊቱ ማንኛውም ግዥ ሲፈጸም ወድድርን መሰረት ያደረገ እንዲሆን የስራ አመራሩ

ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ የመንግስት ግዥ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ እና በአዋጁ የተመለከቱ የግዥ መርሆዎችን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

1.5.1 ግኝት፣ በዋጋ ማቅረቢያ አወዳድሮ መገዛት ሲገባው በቀጥታ የተገዛ፣

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በታህሳስ 12 ቀን 2008ዓ.ም የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 24.2 "ለግንባታ ሥራ እስከ ብር 500,000.00፣ ለዕቃ እስከ ብር 200,000.00፣ ለምክር አገልግሎት እስከ ብር 120,000.00 እና ለሌሎች አገልግሎቶች እስከ ብር 50,000.00 ከዚህ የገንዘብ መጠን የማይበልጥ እና በዋጋ በማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የሚፈፀም ግዥን ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው እንዲፀድቅ በማድረግ ግዥ መፈፀም ይችላል፡፡" የሚል ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቀድሞ ማቀድ እስከ ቻለ ድረሰ ማንኛውንም ግዥ በመመሪያው መሰረት መግዛት ሲገባው በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ መፈፀም የሚገባውን ብር 844,251.15 በቀጥታ ግዥ መፈፀሙን በኦዲት ወቅት ለመመልከት ችለናል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የአቅራቢው ስም	ቀን	የደረሰኝ ቁጥር	የብር መጠን	የወጪ ምክንያት
1	መከላካያ ሠራዊት መኮንኖች ክበብ	09/06/09	BPV-330197	66,555.34	ግንባር ቀደም ሰራተኞች ሽልማት
2	በኢፌዲሪ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የሃይቴክ ኢንጂነረንግ ኢንዱስትሪ	12/10/09	BPV-330004	179,882.56	በቁጥር 14 ፋና ቴሌቪዥን ግዥ
3	ደሳለኝ ሆቴል	16/07/09	BPV-330292	183,090.50	ለ80 ሰው ከክልሎች ጋር የ6 ወር ስብሰባ
4	ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል	16/01/09	BPV-733754	50,600.00	መስተንግዶ አገልግሎት
		02/02/09	BPV-733792	50,340.27	

5	ህብር የአገር ውስጥ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ-ሞጆ-አ.አ	27/12/08	BPV-733717	10,000.00	ትራንስፖርት
		27/12/08	BPV-733717	9,500.00	
6	ትራንስፎርሜሽን ሀገር ውስጥ ደረጃ 3ለ የደ/ጭ/ ማመላለሻ- ሞጆ እስከ አ.አ	09/12/08	BPV-733675	11,000.00	
		16/12/08	BPV-733694	12,000.00	
7	ዳህላክ የሀገር ውስጥ የደ/ጭ/ማ/ ባለንብረት ማህበር-በግለሰብ ደረሰ	16/03/09	BPV-733891	10,000.00	
8	ጊዮን ሆቴል	20/01/09	BPV-733961	21,470.24	መስተንግዶ
9	አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል	11/04/09	BPV-733965	120,203.89	
10	የኢትዮጵያ ሆቴል	24/04/09	BPV-330116	17,752.85	
11	ኤ.ኤም ማተሚያና መሸጊያ ኃ.የተ.የግ.ማህበር /ህዝብ ግንኙነት/	02/05/09	BPV-330133	101,855.50	አጀንዳ የጠረጴዛ ካላንደር እና ማስታወሻ መፃፊያ
			ጠቅላላ ድምር	844,251.15	

1.5.2 ስጋት፤

ቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በዋጋ ማወዳደሪያ መግዛት ሲቻል ያለምንም ውድድር በቀጥታ ግዥ መፈፀም የመንግሥት ገንዘብ ያላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ ከፋች ሊሆን ይችላል፡፡

1.5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

በዋጋ ማቅረቢያ እስከ 200,000.00 መግዛት ሲገባ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቀጥታ ግዥ መፈፀሙ ትክክለኛ አሰራር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ መ/ቤቱ ቀድሞ ማቀድ እስከቻለ ድረስ እና

በዕቅድ ግዥ ውስጥ አካቶ እስኪያዘው ግዥ ሲፈፅም በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ መሰረት ብቻ በተገለጹት የግዥ ዘዴዎች መሠረት በውድድር መሆን አለበት፡፡ ለወደፊቱም የስራ አመራሩ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ የመንግስት ግዥ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ እና በአዋጁ የተመለከቱ የግዥ መርሆዎችን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

1.5.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

1- <u>መከላከያ ሰራዊት መኮንኖች ክበብ</u>

ዕለት ከዕለት የሚከናወኑ ስራዎች አስቸኳይ ግዥ በሚያጋጥምበት ሁኔታ ስራው ካልተሰራ ወይም ካልተከናወነ የባሰ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ጉዳዩ በበላይ ኃላፊ በማስወሰን ግዥው እንዲፈፀም ይደረጋል

1ኛ. ተወዳዳሪዎች በመታጣቱ

2ኛ. የተያዘው ፕሮግራም አስቸኳይ በመሆኑ

3ኛ. ታምኖበት በበላይ ኃላፊ ፈቃድ ግዥው እንዲከናወን የተደረገ

2- <u>በኢፌድሪ ብረታብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የሃይቴክ ኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪ</u>

ፋና ቴሌቪዥን የተገዛበት ሁኔታ

1ኛ. ብቸኛ አምራች በመሆኑ

2ኛ. በገበያ ዝቅተኛ ዋጋ በመሆኑና የመንግስት መ/ቤት መሆኑ ታምኖበት በበላይ ኃላፊ ውሳኔ ተሰጥቶበት እንዲገዛ የተደረገ ነው፡፡

3- <u>ደሳለኝ ሆቴል ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል፣ ጊዮን ሆቴል፤ አዲስ አበባ ሂልተን ሆቴል እና የኢትዮጵያ ሆቴል</u>

በፕሮፎርማ የተከናወነ ግዥ ነው።

4- <u>ህብር የአገር ውስጥ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ሞጆ ኢ.አ፣ትራንስፎርሜሽን ሃገር ውስጥ ደረጃ 3ለ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ሞጆ እስከ ኢ.አ እና ዳህላክ ሃገር ውስጥ ደረጃ 3ለ የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ባለንብረት ማህበር በግለሰብ ደረሰ</u>

ከተራ ቁጥር 5 እስከ 7 ድረስ ላለው ከሞጆ ወደብ ወደ አሸዋ ሜዳ ስቶር በተለያዩ ጊዜያት ኮንቴይነር ተጭኖ የተመላለሰበትን የተከፈለ ክፍያ ከስራው ባህሪ አንፃር ማወዳደር የማይቻል በመሆኑና በለቀማ ግዥ የተከናወነ፡፡

1.5.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ዕለት ከዕለት የሚከናወኑ ስራዎች አስቸኳይ ግዥ በሚያጋጥምበት ሁኔታ ስራው ካልተሰራ ወይም ካልተከናወነ የባሰ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ጉዳዩ በበላይ ኃላፊ እና በፕሮፎርማ የተከናወነ ግዥ ነው ቢልም የተሰጠው ምላሽ ትክክል አይደለም፡፡ ከሰነዱ እንደተረጋገጠው እንድተባለው የተሰጠው ምላሽ በፕሮፎርማ ግዥው ተከናውኖ ቢሆን እንደ ግኝት አይጠየቅም ነበር፡፡ ስለዚህ ለወደፊቱ በግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ብቻ መሰራት አለበት፡፡

1.6.1 ግኝት፣ ግዥን ከፋፍሎ መግዛትን በተመለከተ፣

የፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/01 አንቀፅ 33 ንዑስ አንቀፅ 4 እና በፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 ቁጥር 24 ንዑስ ቁጥር 1 ስር ‹‹በዚህ አዋጅ ወይም በግዢ መመሪያው የተዘረጉ የግዢ ስርዓቶችን ለመሸሽ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዢዎች መከፋፈል እንደሌለባቸው እና የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከቻለ ድረስ ግዥን በጨረታ /በፕሮፎርማ/ የግዢ ዘዴ መጠቀም እንዳለባቸው አዋጁና መመሪያው ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኤ-መንግስት ዳሬክቶሬት በ25/07/2009 ዓ.ም ለሁሉም ክልሎች ለሚገኙ የማህበረሰብ መረጃ ማዕከላት ለማቋቋም 200 የኮምፒውተር ጠረጴዛ ግዥ የተጠየቀ ሲሆን በጥቅል በጨረታ ሂደት መገዛት ሲገባው፣ በአንድ ቀን ከተለያዩ ድርጅቶች በመቆራረጥ በዋጋ ማወዳደሪያ የተገዛ እና የተጠየቀው 200 ሲሆን የተገዛው ግን ብዛት 597 ከመጠየቂያው በ397 የሚበልጥ መሆኑና በሒሳብ መደብ 6313 ብር 991,060.19 ከመመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ መገዛቱን በኦዲታችን ወቅት አረጋግጠናል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	አቅራቢ ድርጅት ስም	ቀን	የደረሰኝ ቁጥር	ጠረጴዛ ብዛት	የገንዘብ መጠን	የወጪ ምክንያት
1	ሞፓርኮ ዩንቨርሳል ኃ/የተ/የግ/ማህበር	19/10/09	BPV-330036	125	199,999.37	የኮምፒዩተር ጠረጴዛ ግዥ
2	ታሪ ነጋ ጀነራል ትሪዲንግ	19/10/09	BPV-330040	124	198,339.32	

3	ዩኒ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	19/10/09	BPV-330039	150	194,700.75	
4	ቴክኖ ስታይል ሴንተር ኃ/የተ/የግ/ማህበር	19/10/09	BPV-330041	129	199,530.75	
5	አርገን ትሪዲንግ	19/10/09	BPV-330038	69	198,490.00	የማናጀር ጠረጴዛና ወንበር ግዥ
ጠቅላላ ድምር				597	991,060.19	

1.6.2 <u>ስጋት</u>፣

በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም አያስገኝም ይህም ቁጠባን ፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማረጋገጥ አይቻልም ፣ ከተጠየቀው በላይ ግዥ መፈፀም የመንግሥትም ገንዘብ ያላግባብ እንዲወጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከተጠየቀው ብዛት ውጭ በመብለጥ ግዥ መፈፀሙ ትክክል አይደለም፡፡ ተጨማሪ ጥያቄ ካለ ሰነዱ ላይ መያያዝ ነበረበት፡፡ የተሰጠው መልስ “ይህም ከፕሮፎርማው ጋር ተያይዟል፡፡” ቢባልም መስረጃው ያልተያያዘና የተገዛውን ያህል አለመጠየቁ ከሰነዱ መረዳት ይቻላል፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የኮምፒውተር ጠረጴዛ በመታጣቱ ምክንያት ለሰስት ዓመት ስራው እንዲቆም በኦዲት ወቅት ምላሽ ቢሰጥም የግዥ ፍላጎቱ የተጠየቀው በ25/07/2009 ዓ.ም መሆኑን ከሰነዱ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህም እንኳን ቢሆን የግዥ ኤጀንሲ በማስፈቀድ ግዥውን መፈፀም ይቻል ነበር፡፡ ስለዚህ የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ አይደለም፡፡ ግዢዎች በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መከናወን ይኖርበታል። ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከተቀመጠው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ውጭ መጠቀም መንግስት ማግኘት ያለበትን ጥቅም ያሳጣል፡፡ በመሆኑም ለወደፊቱ መመሪያውን በማገናዘብ ግዥ እንዲደረግ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.6.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ለሁሉም ክልሎች ለሚገኙ የማህበረሰብ መረጃ አካላት ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ሁሉ ተሟልተው የኮምፒውተር ጠረጴዛ በመታጣቱ ምንክያት ለሶስት ዓመት ስራው እንዲቆም አድርጎታል፡፡

<u>የነበረው ሂደት</u>

- ዕቃው መቅረብ የነበረበት በግዥ ማዕቀፍ ቢሆንም የተመደቡ አቅራቢዎች ዕቃውን ሊያቀርቡ አልቻሉም፡፡
- ግልፅ ጨረታ ወጥቶ ለመግዛት ተሞክሮ በዕቃው ብዛትና ለሚፈለገው ስፔሲፊኬሽን ሊገኝ ባለመቻሉ፡፡
- አነስተኛና ጥቃቅን ተፈልገው በበላይ አካል ውሳኔ በውስን ጨረታ አወዳድረን ዋጋ እንዲያቀርቡ ቢደረግም የተጋነነ ዋጋ በመቅረቡ እነዲሰረዝ በመደረጉ ስራው ያልተሰራበት ምክንያት እስከ ፓርላማ ድረስ በሪፖርት ቀርቦ በመስሪያቤቱ በአስቸኳይ መፍትሄ እንዲሰጠው በሚል በተሰጠ መመሪያ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ማኔጅመንት በጉዳዩ ከተወያየ በኋላ በፕሮፎርማ እና በለቀማ በአስቸኳይ ተገዝቶ እንዲሟላ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት እንዲገዛ ተደርጓል፡፡ የክልሎች ፍላጎት ድልድል መሰረት ከተጠየቀው ክፍል የግዥ ፍላጎት ጋር ተያይዟል፡

1.6.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከላይ የተገለፀውን የግዥ ሂደት ያለፈበትን ቢገልፅም በወቅቱ ሂደቱን የሚገልፅ ማስረጃ ያላቀረበ ከመሆኑም የግዥ መጠየቂያን በተመለከተ ተያይዟል ቢባልም ከተጠቀሰው ውጭ በወቅቱም ያልቀረበ እና በመውጫም ውይይት ወቅት እንዳለ ቢገፅም ከውይይቱ በሃላም ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ ለወደፊቱ መሰል ስህተት እንዳይከሰት ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

1.7.1 ግኝት፣ የተሟላ ማስረጃ ሳይኖር የተከፈለ፣

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በሚለው ስር ንዑስ አንቀጽ 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው (ኦርጅናል) ደረሰኝ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግን በተለያየ ቦታ በሚያደርገው የስልጠና እና የስብሰባ መስተንግዶ ወጪ ከማድረጉ በፊት የተሳታፊዎች ዝርዝር፣ ስለመሳተፋቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ማስረጃ ዋና ሰነድ ስለመሟላቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በድምሩ ብር 3,258,398.86 እነማን እንደተሳተፉ ማስረጃ ባልቀረበበት ክፍያዎች ተፈፅመው ተገኝተዋል፡፡

1.7.2 ስጋት፣

ክፍያውም ትክክለኛነት ላያሳይ እና ከተገኘው አገልግሎት በላይ ክፍያ ሊፈፀም ይችላል፡፡

1.7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲቲዩት ጋር የሚደረጉ ቀድሞ በዕቅድ የተያዙ ከየስራ ክፍሉ ተወጣጥተው የሚሔዱትን ቀድሞ እንዲሰለጥኑ የተላኩበት መያያዝ ይኖርበታል፡፡ ለተገኘው አገልግሎት በትክክለኛው ማስረጃ ሳይደገፍ እንደወጪ ሂሳብ መመዝገቡ እና መከፈሉ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ስለማይቻል ደጋፊ ሰነድ ሳይኖር ሂሳብ መከፈል የለበትም፡፡ ልሎች ስልጠናዎችም ሆኑ ስብሰባ ሲደረግ የስራ ክፍሉም ስለወጪው የተሟላ መረጃ ሳይኖር ክፍያ መፈፀም የለበትም፡፡

1.7.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

ወጪዎች ከ8/ስምንት/ ድርጅቶች በ20 / ሃያ /የክፍያ ሰነዶች የተደረጉ ወጪዎች ተደምሮ ሲሆኑ እነዚህም መሟላት የሚገባቸው ሰነዶች በሙሉ መያያዛቸው ተረጋግጦ የተከፈሉ ክፍያዎች ሲሆኑ በኦዲት ምርመራ ወቅት ተያይዞ ያልተገኘው በስብሰባ ወቅት የተያዙ አቴንዳስ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም በሥራ ክፍሉ እየተያዘ ወደፋይናንስ ባለመምጣቱ ነው በምርመራ ወቅት በተሰጠን አስተያየት በአሁኑ ጊዜ አቴንዳሱንም የመረጃው አካል በማድረግ በመሥራት ላይ እንገኛለን፡፡

1.8.1 ግኝት፣ ባልተፈቀደ በጀት ለድጋፍ (ስፖንሰር) የተከፈለ

የፌዴራል መንግስት መመሪያ 4/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ "የመንግስት መ/ቤቶች በጀት ክፍያ የሚፈፅመው ወይም ወጪ የሚያደርገው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው" ይላል፡፡ እንዲሁም የወጪ ሂሳቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት በተገቢው የሂሳብ መደብ የሚመዘገቡ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በዚህ መመሪያዎች መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስንመለከት፡-

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዋልታ ኢንፎሜሽን ማዕከል፣ ምስንዳእ ጋዜጣ ወይን፣ የድሬዳዋ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እና የባህር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር እስፖንሰር በማድረግ በድምሩ ብር 1,243,936.00 ያለ ሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ብር 12,789,120.84 ያለ ሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ መገኘቱ፣
- የካፒታል በጀት ቋሚ ሀብት ለማፍራት ወይም ለማሻሻል የሚወጣ የሚመደብ በጀት ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለመደበኛ ስራ ለመስተንግዶ ወጪ ከዕለት ለዕለት ለስራ ማስኪያጅ ብር 2,418,153.79 ከካፒታል በጀት ላይ ባልተፈቀደ የሂሳብ መደብ መጠቀሙን በኦዲት ወቅት አረጋግጠናል፡፡

1.8.2 ስጋት፣

የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን እና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣው የበጀት ህጉንም ያልተከተለ ከመሆኑም በተጨማሪም የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

1.8.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን በዕቅድ ለተያዙ ሥራዎች መሆኑን አውቆና ተገንዝቦ በበጀት የሂሳብ መደብ ላልተካተተ ወጪ ክፍያ መፈጸም አይኖርበትም፡፡ የመንግስት መስሪያ ቤት ድጋፍ (ስፖንሰር) ማድረግ የሚችል ከሆነ በጀቱ በሂሳብ መደብ 6412 ለድጋፍ (ስፖንሰር) ይታወጅ ነበር፡፡ ሆኖም የተከፈለው ለድጋፍ (ስፖንሰር) ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኦዲት ወቅት ሲመልስ ቀድሞ በበጀት የተያዘ በማስታወቂያ 6253

ስለሆነ በዚያ ነው የተከፈለው ቢባልም ተከፍሎ የተገኘው ለድጋፍ (ስፖንሰር) ስለሆነ ትክክለኛ መልስ አይደለም፡፡ እንደተባለው ቀድሞ በማስታወቂያ የሂሳን መደብ የተያዘ እንኳን ቢሆን በህጉ መሰረት የግዥ ሒደቱን መከተል ነበረበት፡፡ መታየት ያለበት የተደለደለና የተፈቀደ በጀት ሳይኖር በሌላ የሂሳብ መደብ ወጪ ማድረግ ስለማይቻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚያደርጋቸው ግብይቶች የመንግሥት ህግንና መመሪያውን ጠብቆ መስራት አለበት፡፡

ለካፒታል የተመደበው በጀት ለመደበኛ ስራ ለመስተንግዶ፣ ለስብሰባ መጠቀሙ ትክክለኛ ሳላልሆነ ለወደፊቱ በጀት ሲታቀድ በትክክለኛ የሒሳብ መደብ በማቀድ እንዲደለደልለት ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ስለዚህ ለሚቀጥለው ጊዜ መሰል ስህተቶች እንዳይከሰቱ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

1.8.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ለድጋፍ (ስፖንሰር) እና ያለሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ የተገኘ ተብሎ የተጠቀሰውን በተመለከተ በኦዲት ወቅት የተሰጠ ምላሽ ላይ በዝርዝር ለመግለጽ ተሞክሩል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ የማሻሻያ ሃሳብ ላይ የተጠቀሱትን በሚቀጥለው መደገም የሌለባቸውን እንዳይከሰቱ ንቃቄ እንደደረግ የተሰጠውን አስተያየት ተቀብለን ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡

1.9.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ያለደንብና መመሪያ ለሽልማት የተፈጸመ ክፍያ፣</u>

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን13/8/03 ባስተላለፈው መመሪያ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ /በቦርዱ/ የሰራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማሻሻል፣ መለወጥ ወይም አዲስ መፍቀድ እንደማይችልና እስከ አሁን የተከናወኑም ካሉ ትክክል እንዳልሆነ የተወሰነ መሆኑ እና ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የደመወዝ ስኬሎች እና ጥቅማ ጥቅሞች በአስቸኳይ እንዲቋረጡ ወስኗል፡፡ በዚህም መሰረት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ኦዲት ሲደረግ ግንባር ቀደም ፈጻሚዎች ለማበረታታት በሚል ከስራ ክፍሎች ግንባር ቀደም ፈጻሚ በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 733892 በ16/03/2009 በሂሳብ መደብ 5054 ለ45 ፈጻሚና ለ4 የስራ ክፍል ኃላፊዎች በአጠቃላይ 49 ከመያዣ ሂሳብ መደብ 5054 (የሌሎች የመያዣ ሂሳቦች) ተከፋይ ሂሳብ በ2005/6 የበጀት ዓመት ከግል ዘርፍ የስፖንሰር ሽፕ ገቢ በማለት ብር 245,000,00 ለቦንድ ሽልማት እንዲያገኙ መደረጉን ነገር ግን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ

በ5054 የሌሎች የመያዣ ሂሳቦች ላይ ሳይሆን ክፍያውን የፈፀመው ከበጀት ላይ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

1.9.2 <u>ስጋት</u>፣

ከመመሪያና ደንብ ውጭ ክፍያዎችን መፈፀም የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ የሚከፍት አሠራር ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

1.9.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት ስጦታ ወይም ሽልማት መስጠቱ አግባብነት ስለሌለው ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ "**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከያዘው በጀት ቀንሶ ሳይሆን ከስፖንሰር ሽፕ ከተገኘ ገቢ ነው እንዲከፈል የተደረገው፡፡**" ተብሎ የተመለሰው መልስ ከ5054 (የሌሎች የመያዣ ሂሳቦች) ላይ ቀድሞ ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በዓመቱ መጨረሻ ፈሰስ ከሆነ በኃላ ተጠይቆ ያልመጣ ስለሆነ ትክክለኛ መልስ አይደለም፡፡ ስለዚህ ለወደፊቱ እንደዚህ ያለ ስህተት እንዳይፈፀም ሚኒስር መስሪያ ቤቱ የእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

1.9.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

ለግንባር ቀደም ሰራተኞች የተፈጸመው የማበረታቻ ክፍያ ከመደበኛ በጀት ሳይሆን ከስፖንሰርሽፕ ከተገኘ ገንዘብ ነው የህዳሴ ግድብ ቦንድ በመግዛት ሽልማቱ እንዲፈጸም የተደረገው፡፡ ክፍያውም በገንዘብ ለእያንዳንዱ ተሸላሚ የተሰጠ ሳይሆን የህዳሴ ግድቡን ለመደገፍ ቦንድ በመግዛት አገርም እየጠቀሙ ለስራተኛውም ማበረታቻ እንደሆን የተደረገ መሆኑን እየገለጽን የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር በሁሉም ተቋማት ዘንድ ወጥነት ያለው የማበረታቻ ስርአት እስኪዘረጋና መመሪያ እስኪወጣ ድረስ ይቁም ካለ በኋላ ግን ሚኒስቴር መ/ቤታችንም መመሪያዉን ተከትሎ ያቆመበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ቀደም ሲል ሲሰራበት እንደነበረው በውጤት ተኮር የአሰራር ስርአት መሰረት ውጤታማ ሰራተኞችን የማበረታቱ ስራ በወቅቱ ትክክል ስለነበር ነው፡፡

1.10.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>የጨረታ ሂደት ተከትሎ ያልተፈጸመ ግዥ</u>፣

የፌዴራል መንግስት ግዥ አፈፃፀም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ክፍል 4 አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 4 በመንግስት መ/ቤት ከግልፅ ጨረታ ውጪ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የግዥ ለመጠቀም የተመረጠበትን

ምክንያት እና ሁኔታዎች የሚገልፅ ሰነድ መያዝ እንደሚኖርበት ተደንግጓል፤ እንዲሁም በዚህ መመሪያው ክፍል 8 አንቀፅ 31/1 ደግሞ መደበኛ ባልሆኑ የግዥ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በመመሪያው ላይ የተዘረዘሩትን የግዥ አፈጻፀም ሥርዓቶች ሊጠበቁ ካልቻሉ ወይም መደበኛ ያልሆኑ ግዥ መፈፀም የሚችሉት በአዋጁ አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 5 መሰረት ለኤጀንሲው አቅርበው ሲፈቀድ ብቻ መሆን እንዳለበት ተመልክቷል፤ ነገር ግን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለግዥው ኤጀንሲው አቅርበው ሳያስፈቅዱ እና የግዥ ዘዴውም የተመረጠበት ምክንያት እና ሁኔታ ሳይገለፅ በተለያዩ የግዥ ዘዴ መፈፀሙ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ካየናቸው ውስጥ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

1. ለConsultancy services for development of Ethiopian national E-commerce platform ለተሸጠው የግዥ ጨረታ ሰነድ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-
    - ሌሎች ተጫራቾች እያሉ በጨረታ ያልተሳተፈ እና የጨረታ ሰነድ ያልገዛ Grail consulting Service Pvt.Ltd የተባለ ድርጅት እንደተሳታፊ አድረጎ ማቅረቡን፣
    - አሸናፊ ያልሆነ ድርጅት ማለትም Grail consulting Service Pvt.Ltd በብር 5,714,521.05 Letterr of Credit እንዲከፍት ማድረጉን፣
    - የፓርትነር ማስረጃ ሳይቀርብ ከPERAGO INFORMATION SYSTEMS PLC ከተባለው ድርጅት ፓርትነር ናቸው በማለት ብር 1,459,124.02 የተከፈለ መሆኑን፣
    - እንዲሁም ድርጅቶቹ የባንክ ጋራንቲ እና ሲፒኦ በወቅቱ ስለማቅረባቸው ማስረጃ ያልተያያዘ መሆኑን፣

  በድምሩ ብር 7,173,645.07 የግዥ ሂደቱን ሳይከተል ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን፣

2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ Consultancy services for development of Online content Regulation framework for Ethiopia ለወጣው ጨረታ የመነሻ ገንዘቡ ሳይታወቅ አሸናፊ ተበሎ የተገለጸዉ ድርጅት እያለ መነሻ ገንዘቡ ላልታወቀ ድርጅት ከድርጅቱ ጋር ሲወዳደር ለነበረዉ ለLeading Assocciation ብር 931,930.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑን እና በተጨማሪም የፓርትነር ማረጋጋጫ ሳየይቀርብ Leading Assocciation ከ Grail consulting Service Pvt.Ltd ጋር ፓርትነር ናቸው በማለት ለGrail consulting Service

Pvt.Ltd ደግሞ ብር 3,036,770.94 (በዶላር 116,000.00 USD) Letterr of Credit ለመክፈት ወደ ባንክ ተቀማጭ መደረጉን፣

3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ Development of online Customer Compliant and Suggestion Management System ለወጣው ጨረታ የቴክኒክ ግምገማውን የሚያሟላው ብቸኛ አሸናፊ በሚል PERAGO INFORMATION SYSTEMS PLC በብር 3,489,675.00 ውል የፈጸመ ሲሆን፣ ከድርጅቱ ጋር የቴክኒክ ውድድር ያደረገው Custor Computing PLC ምን ያህል ዋጋ እንዳቀረበ ሳይታይ የፋይናንሻል ኦዲት ሪፖርት ያላቀረበ መሆኑን በቴክኒክ ግምገማው በመጥቀስ ካለምንም የዋጋ ማነፃፀሪያ እና የገበያ ዋጋ ጥናት ማስረጃ ባልቀረበበት ግዥ መካሄዱ፣

4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ Development of electronic public procurement system በቴክኒክ ግምገማ ያለፉት ድርጅቶች በፋይናንሻል ሲወዳደሩ CSM/Africom Technologies ያቀረበው ብር 3,477,600.00 ሲሆን፣ PERAGO INFORMATION SYSTEMS PLC ያቀረበው ደግሞ ብር 3,501,922.50 በመሆኑ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 8÷ሀ መሰረት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው CSM/Africom Technologies ማለፍ ሲገባው PERAGO INFORMATION SYSTEMS PLC እንዲያልፍ መደረጉ፣

5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ Content Management System with SOA Training የግልፅ ጨረታ ወጥቶ በውድድሩ በብር 386,400.00 ያሸነፈው Sysmbol Technologies የአሰልጣኝ ለውጥ በማድረጉ መ/ቤቱ ያልተቀበለው ሲሆን፣ ሁለተኛ ዝቅተኛ ያቀረበው E-System Africa ብር 661,250.00 መመረጥ ሲገባው፣ ለITSC PLC በብር 744,625.00 እንዲመረጥ መደረጉና የተፈለገው አሰልጣኝ ስለማሟላቱ ሳይረጋገጥ እንዲሠራ መደረጉ፣

6. ሚኒስቴር መ/ቤቱ Support and Maintenance of Government Portals and 129 Information eService's ግልፅ ጨረታ እንዳወጣና ብቸኛ ተወዳዳሪ እንደሆነ በመግለፅ ከE-Systems Africa ላቀረበው ዋጋ ብር 7,015,000.00 ከገበያ ጋር ስለመቀራረቡ ዋጋ ሳይጠና ከተያዘው በጀት ብር 6,900,000.00 ጋር በማነፃፀር ውል የተገባ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ላልተወዳደረውና ውል ላልገባው ለግስላ ጀነራል ቢዝነስ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ድርጅት በበጀት ዓመቱ ከታየው ውስጥ ብር 2,860,941.25 የተከፈለ መሆኑ፣

7. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዳታ ማዕከሉ ጥገና እንዲከናወን በቀረበው ፍላጎት ግልፅ ጨረታ ለማውጣት ጊዜ ስለሚወስድ በማለት በውስን ጨረታ ድርጅቶችን በመጋበዝ ከሳሙኤል አሰፋ የሕንፃ ሥራ ተቋራጭ ብር 5,926,525.00 የጥገና ግዥ የተፈፀመ መሆኑ፣ በተጨማሪም በተለያዩ ወረዳዎች የሚገኙ የኮሙኒቲ ሬዲዮኖች በጊዜው ተወዳድሮ ስራውን ያሸነፈው ድርጅትየሳውንድ ፕሩፍ እና የፊኒሽንግ ስራዎችን ሳያጠናቅቅ ጥሎ በመሄዱ በማለት ስራውን ለመጨረስ በቀጥታ ግዥ ብር 5,692,500.02 ለዚሁ ድርጅት የተሰጠ መሆኑን፣
8. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የማከራየት ፍቃድ ካለው ድርጅት የመኪና ኪራይ አገልግሎት ግዥ መፈፀም ሲገባው የህዝብ ማመላለሻ የግል ትራንስፖርት ማህበር ፍቃድ ካለው ድርጅት ጋር የትራንስፖርር ኪራይ ላቀረበበት በማለት የግዥ ሂደቱን ያልተከተለና የንግድ ፍቃድ ለሌለው ብር 1,598,780.00 የተከፈለ መሆኑን፣

1.10.2 <u>ስጋት</u>፣

በዘርፉ የተሰማሩ ሌሎች ተወዳዳሪዎች ፍትሀዊ የሆነ የንግድ ውድድር እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.10.3 **<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>**

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በምላሹ ላይ የመለሰው ምልሽ " የጨረታ ሰነድ ያልገዛው ቀደም ሲል ገዝቶ የተወዳደረ ሲሆን በዚህ መሰረት በአንድ ጨረታ አንድ ድርጅት ተመሰሳይ ጨረታ ድጋሚ ገንዘብ ማስከፈል ተገቢ ባለመሆኑና የንግድ የሚያስመስል በመሆኑ፣ ብቸኛ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ ድርጅት በመሆኑ፣ በ20/80 በሚለው ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ አሸናፊ ሆኖ የተቀመጠው በመሆኑ፣ ብቸኛ በመሆኑ ከገበያ ዋጋ በላይ እንዳይቀርብ የሰራ ክፍሉ የገበያ ጥና አድርጎ ዋጋ እነዲያረጋግጥ በመደረጉና አንድ ተወዳዳሪም ቢሆንም መ/ቤቱ ካመነበት ግዥውን መፈፀም ይቻላል፣ የግዥ ዘዴ ውስጥ ውስን ጨረታ የሚፈቀድ በመሆኑእና የታሰረው ውል ግዜው ካበቃ በኋላ ለግዥ ኤጀንሲ ተጨማሪ ጊዜ እነዲሰጠን በበላይ ኃላፊ በደብዳቤ ተጠይቆ ችግሩ ታምኖበት ለ2 ዓመት በማዕቀፍ ግዥ እንድንጠቀም ተፈቅዷል፡፡ በጠቅላላ በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ተከትሎ ግዥው መፈፀሙ ቢገለፅም የተሰጠው ምላሽ ትክክለኛ ያለሆነና የግዥ አዋጁን የተከተለ አለመሆኑ በኦዲት ውት ተረጋግጧል፡፡ ማናቸውም የግዥ ውሣኔ የሚሰጥበት መስፈርት እና በእያንዳንዱ ግዥ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ ጉዳይ ለሚመለከታቸው ሁሉ ግልፅ እና ፍትሐዊ መሆኑን የመስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊ

ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዘርፉ የተሰማሩ ሌሎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች ተመጣጣኝ የመወዳደር ዕድል መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

1.10.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

1. ጨረታው November 13/2015 ወጥቶ ሰነዱን 17 ድርጅች ቢገዙም በዕለቱ ሰነድ ገቢ ያደረገው 1 ድርጅት ገሬል ኮንሰልቲንግ ብቻ ቢሆንም አንድ ተወዳዳሪ ብቻ በማቅረቡ በቀጣይ ጨረታው በድጋሚ እንዲወጣ በማድረግ January 2016 ወጥቶ ሰነዱን 9 ድርጅቶች ገዝተው በጨረታ ማስገቢያው ዕለት 3 ድርጅቶች ሰነድ አስገብተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ቴክኒካል ግምገማ ላይ 2 ድርጅቶቸ አልፈው ወደ ቀጣይ የግዥ ሂደት በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ተከትሎ ተከናውኗል፡፡ ፔራጎ ድጋሚ የጨረታ ሰነድ ያልገዛው ቀደም ሲል ገዝቶ የተወዳደረ ሲሆን በዚህ መሰረት በአንድ ጨረታ አንድ ድርጅት ተመሳሳይ ጨረታ ድጋሚ ገንዘብ ማስከፈል ተገቢ ባለመሆኑና የንግድ የሚያስመስል በመሆኑ መጀመሪያ በገዛው ጨረታ እንዳለ ታውቆ እንዲወዳደር ተደርጓል፡፡
2. Consultancy services for development of Online content Regulation framework for Ethiopia
   - በሄራልድ ጋዜጣ December 25/2015 በወጣው ጋዜጣ ላይ ግልፅ ጨረታ እንደታወጀ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡
   - 8 ተወዳዳሪዎች ሰነዱን ገዝተዋል፡፡
   - ጨረታውን የተሳተፉት 4 ተወዳዳሪ ድርጅቶች ተሳትፈዋል፡፡በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ተከትሎ ግዥው የተፈፀመ፡፡
3. Development of Online Customer Compliant and Suggestion Management System
   - በሄራልድ ጋዜጣ መስከረም 20/2015 በወጣው ጋዜጣ ላይ ግልፅ ጨረታ እንደታወጀ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡
   - 5 ተወዳዳሪዎች ሰነዱን ገዝተዋል፡፡
   - ጨረታውን የተሳተፉት 5 ተወዳዳሪ ድርጅቶች ተሳትፈዋል፡፡
   - በቴክኒካል ገምገማ ላይ 5 ድርጅቶች ለግምገማ ቀርበው አንድ ድርጅት ብቻ ቴክኒካሉን እንዳሟላ የቴክኒክ ኮሚቴው በቴክኒክ ሂደቱ ላይ ኢቫሉዌሽን ሰርቶ

አቅርቧል በዚሁ መሰረት አሸናፊ የሆነው ፔራጎ የተባለው ድርጅት ነው፡፡ በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ተከትሎ ግዥው የተፈፀመ፡፡

4. Development of electronic public procurement system
   - በሄራልድ ጋዜጣ November 12/2014 በወጣው ጋዜጣ ላይ ግልፅ ጨረታ እንደታወጀ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡
   - 11 ተወዳዳሪዎች ሰነዱን ገዝተዋል፡፡
   - ጨረታውን የተሳተፉት 3 ተወዳዳሪ ድርጅቶች ተሳትፈዋል፡፡
   - ለPERAGO INFORMATION SYSTEMS PLC አሸናፊ ሊሆንበት የቻለው ውድድሩ በዝቅተኛ ዋጋ ሳይሆን 20/80 በሚለው በኮንሰልታንት ግዥ ሲሆን አሸናፊ የሚሆነው በቴክኒክ ሂደቱ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበ ነው፡፡ ስለዚህ በዚሁ መሰረት ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ አዋጅና መመሪያ መሰረት ባደረገ ግዥው የተፈፀመ ነው፡፡

5. Content Management System with SOA Training ለ ITSC PLC አሸናፊ ሊሆንበት የቻለው ውድድሩ በዝቅተኛ ዋጋ ሳይሆን 20/80 በሚለው ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ አሸናፊ ሆኖ የተቀመጠው ITSC PLC በመሆኑ በቴክኒክ ሂደቱ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበ ነው፡፡ ስለዚህ በዚሁ መሰረት ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ አዋጅና መመሪያ መሰረት ባደረገ ግዥው የተፈፀመ ነው፡፡

6. Support and Maintenance of Government Portals and 129 Information eService's
   - በሄራልድ ጋዜጣ መስከረም 20/2015 በወጣው ጋዜጣ ላይ ግልፅ ጨረታ እንደታወጀ ከፋይሉ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡
   - በተደጋጋሚ ለ ሶስት ጊዜ ግልፅ ጨረታ ወጥቶ አቅራቢ አልተገኘለትም
   - ብቸኛ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ ድርጅት ነው፡፡
   - በጨረታው ብቸኛ ተወዳዳሪ መሆኑን የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ አይቶ ወደ ቀጣይ እንዲያልፍ ውኔ ሰጥቶበታል፡፡
   - ብቸኛ በመሆኑ ከገበያ ዋጋ በላይ እንዳይቀርብ የሰራ ክፍሉ የገበያ ጥና አድርጎ ዋጋ እነዲያረጋግጥ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት የሰራ ክፍሉ ዋጋ እንዲያረጋግጥ ተደርጓል፡፡በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት አንድ ተወዳዳሪም ቢሆን መ/ቤቱ ካመነበት

ግዥውን መፈፀም ይቻላል በፈቀደው መሰረት መ/ቤቱ ሁኔታውን አረጋግጦ በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ግዥው እንዲፈፀም ተደርጓል፡፡

7. በቤተ መንግስት ውስጥ ለሚገኘው ብሄራዊ የዳታ ማዕከል ስራና ሙሉ ዕድሳት ለማሰራት በተደጋገሚ በግልፅ ጨረታ ወጥቶ ተወዳዳሪ የታጣለት እና በመጨረሻም ችግሩ ለበላይ ኃላፊ ቀርቦ ተወዳዳሪ ድርጅቶች በውስን ጨረታ ተጫርተው ስራው እንዲሰራ በተፈቀደው መሰረት የተከናወነ ስራ ነው፡፡ ለዚህም በተፈቀደው የግዥ ዘዴ ውስጥ ውስን ጨረታ የሚፈቀድ በመሆኑ ነው ውስን ጨረታ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎችም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

<u>የውስን ጨረታ ግዥ አፈፃፀም</u>

1. ተወዳዳሪ ድርጅቶች (የዕቃው አቅራቢዎች) የተወሰኑ ሲሆኑ ፡-
2. የገንዘቡ መጠን በውስን ጨረታ (Trush Hold) መጠን ሆኖ ሲገኝና በበላይ አካል ሲፈቀድ፡-
3. በተደጋጋሚ በግልፅ ጨረታ ከሁለት ጊዜ በላይ አየር ላይ ውሎ ተወዳዳሪ ሳይገኝለት ሲቀር፡- ይህንን መሰረት ባደረገ በውስን ጨረታ ግዥው የተፈፀመ፡፡

8. ንጉሴ ተፈራ የህዝብ ማመላለሻ የግል ትራንስፖርት ማህበር ህዳር 4/2008 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣው የግልፅ ጨረታ መሰረት 29 ተወዳዳሪ ድርጅቶች ሰነድ የገዙ ሲሆን በጨረታ መክፈቻው ዕለት 11 ተወዳዳሪ ድርጅቶች ሰነዱን አስገብተዋል፡፡

በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት ኢቫሉዌሽን ተሰርቶ አሸናፊ ድርጅት ከተለየ በኋላ ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ቀርቦ ከተወሰነ በኋላ ስራው እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

የታሰረው ውል ግዜው ካበቃ በኋላ ለግዥ ኤጀንሲ ተጨማሪ ጊዜ እነዲሰጠን በበላይ ኃላፊ በደብዳቤ ተጠይቆ ችግሩ ታምኖበት ለ2 ዓመት በማዕቀፍ ግዥ እንድንጠቀም ተፈቅዷል፡፡

1.10.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም በውስን ጨረታ ለማሳተፍ ቀድሞ የተቀመጡ የግዥ ዘዴዎችን መጠቀም ይገባ ነበር፣ ብቸኛ ተወዳዳሪ ለመሆኑ በሚመለከተው አካል ማረጋገጫ መቅረብ ነበረበት፣ አንድ ተወዳዳሪ ሲሆን ከሚመለከተው አካል ወይም ያለው የገበያ ዋጋ ስንት እንደሆነ የሚያስረዳ ማረጋጋጫ መቅረብ ያበት ሲሆን ብቸኛ ለመሆን በጀት መሰረት መደረግ የለበትም እንዲሁም ያሸነፈው ድርጅት ስራውን በሌላ ሦስተኛ ወገን እያሰራ ስለመሆኑ ሰነዱ ያስረዳል፣ ቀድሞ ባልወጣ መመዘኛ 20/80 ባላተገለፀበት ሆኔታ

እሱን መሰረት ተደርጎ ነው ተብሎ የተሰጠው ምላሽ ታማኝነት የለውም፤ የግዥና ንብረት አስተዳዳር ኤጀንሲ ባልፈቀደበት እንደ ፈቀደ አድርጎ ምልሽ መስጠት ትክክል ያለሆነ ስለሆነ በጠቅላላ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለወደፊቱ በግዥ ላይ የሚያደርገውን ሂደት መከታተልና የሚታየውን ክፍተተት በአስቸኳይ ማስተካከል ይጠበቅበታል፡፡

2. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

2.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በሪፖርቱ እና በዝርዝር ቋቱ የታየው የተሰብሳቢ ሂሳብ ልዩነት፣</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ (ለ) "የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ7 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት" እና በንዑስ አንቀጽ (መ) "ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ" መመሪያው ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-

- ሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በድምሩ ብር 212,154,657.39 ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ ሲሆን፣ የዝርዝር መነሻ ቋት ድምር ግን ብር 210,936,066.58 በመሆኑ ከመነሻ ሂሳብ ወይም ከመወራረጃ ሰነዱ ጋር ሲገናዘብ፣ ልዩነት ብር 1,218,590.81 ሪፖርቱ በመብለጥ የሚታይ መሆኑን፡-
- የዝርዝር መነሻ ቋት ውስጥ ብር 64,094.00 ከለቀቁ ሰራተኞች ያልተሰበሰበ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2.2 <u>ስጋት፣</u>

ተሰብሳቢ ሂሳብ በተቀመጠለት መመሪያ መሰረት ካልተወራረደ የመንግስት ገንዘብ ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊያደርስ ይችላል፡፡

በባንክ የሚታየው Letterr of Credit ሳይከፈት ለዓመታት መቀመጡ ተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲበዛ፣ በቂ ምዝገባም ላይደረግ እና ክትትል ላይደረግ ይችላል፡፡

2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- አንደ ተሰብሳቢ የተያዙት ሂሳቦች ያሉበት ደረጃ እና ያለው ልዩነት ተጣርቱ በተጠቃለለው የሂሳብ ሪፖርት ላይ የቀረበው ማስረጃ ሊታረቅ ይገባል፡፡

- እንዲሁም ከለቀቁ ሰራተኞች የሚፈለገው ተሰብሳቢ ሂሳብ ተከታትሎ መሰብሰብ ይገባል፡፡ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ እና በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምት እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰብሳቢ ሂስብ ክምችት እንዳይኖር አመራሩ ክትትል፣ ቁጥጥር ማድረግ እና ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

- የተሰብሳቢ ሂሳብ ልዩነት ተብሎ ለተጠቀሰው ሂሳብ መግለጫው ሪፖርት ድምርና የዝርዝር መነሻ ቋት ድምር ልዩነት ይታያል ተብሎ የተጠቀሰው የሂሳብ መግለጫው ሪፖርት ድምር 212,154,657.39 ሲሆን ዝርዝር በየአካውንት ኮዱ የተቀመጠወም ድምር የገጠመ እና ብር 212,154,657.39 መሆኑን እየገለጽን መረጃውን 8/ስምንት/ ገጽ በአሁኑ ወቅት አያይዘን አቅርበናል፡፡ የተሰጠውንም አስተያየት ተቀብለን ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡
- በተለያዩ ጊዜያት የሚፈለግባቸው ንብረትና የገንዘብ እዳ የሌለባቸው ስለመሆኑ ክሊራንስ ሳያዞሩና ማረጋገጫ ሳይወስዱ ከስራ ስለሚጠፉ ሰራተኞች ጉዳይ በህግ አግባብ ገንዘቡ እንዲመለስ ለማድረግ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው፡፡ ስለሆነም በመ/ቤቱ ልዩ ልዩ የስራ መደቦች ላይ ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩና ክሊራንስ ሳይወስዱ የጠፉ ሰራተኞች ያለ አግባብ የወሰዱትን ገንዘብ በህግ አግባብ ለማስመለስ ማስረጃዎችን የማደራጀት ስራዎች ተሰርተው ጉዳዩ በህግ ዳይሬክቶሬት በኩል እየተኬደበት ይገኛል፡፡

3. <u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

3.1 <u>ግኝት፣</u> <u>በሪፖርቱ እና በዝርዝር መነሻ ቋት የታየው የተከፋይ ሂሳብ ልዩነት፣</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ (ሀ) “ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለበት” እና በንዑስ አንቀጽ (ሐ) “መ/ቤቶች ከተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የመያዥያ ሂሳብ፣ የግብርና

ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለባቸው" መመሪያው የሚያዝ ቢሆንም፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ፡-

- የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በድምሩ ብር 53,945,245.34 ተከፋይ ሂሳብ የሚታይ ሲሆን፣ የዝርዝር መነሻ ቋት ድምር ግን ብር 53,988,399.20 በመሆኑ ከመነሻ ሂሳብ ወይም ከመወራረጃ ሰነዱ ጋር ሲገናዘብ፣ ልዩነት ብር 43,153.86 የዝርዝር መነሻ ቋት በመብለጥ የሚታይ መሆኑን፡-
- እንዲሁም ከዝርዝር መነሻ ቋት ውስጥ ብር 133,297.16 በሂሳብ መደብ 5058 (የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ) የተመዘገበ ሲሆን ገንዘቡ በዕዳነት የተያዘበት/የተመዘገበበት ቀን፣ ወርና ዓ.ም የሌለውና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባለበጀት መ/ቤት ሆኖ ሳለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ መታየቱ የሂሳቡን ትክክለኛት አያሳይም፡፡

3.2 <u>ስጋት፣</u>

- የሚቀነሱ የተለያዩ ተቀናናሽ ሂሳቦች ለተጠቃሚዎቹ በወቅቱ ገቢ አለማድረግ (አለመክፈል) ገንዘቡ ከዕቅድ ውጭ ለሆነ ሥራ እንዲውል መንገድ ከመክፈቱም በተጨማሪ ለበጀት ክትትልን ቁጥጥር አመቺ አይደለም፡፡
- በተሰብሳቢ ሂሳብነት የተያዘው የመያዥያ ሂሳብ ለለማን ለማን እንደሚከፈልና የተያዘው ገንዘብ ልዩነት ላይታወቅ ይችላል፡፡

3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የሚቀነሱ ሂሳቦች ወዲያውኑ ለተጠቃሚዎቹ እንዲከፈሉ፤ በሥራ እንቅስቃሴው የሚሰበሰበው ታክስ መንግሥት በዕቅድ ለያዛቸው ልማት ሥራዎች እንዲውል በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ፤ በግንባታ ዘርፍ ከክፍያ ሂሳብ ላይ በመያዥያነት የተያዘው ገንዘብ ከማን ከማን ምን ያህል እንደሆነ የመነሻ ዝርዝር ቋት እንዲኖረው ማድረግ አለበት፡፡ ስለዚህ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሂሳቡ ያለበትን ደረጃ ከመነሻ መዝገቦ መያዝ እና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ በማድረግ በአጠቃላይ ተከፋይ ሂሳቦች ለማን ለምን እንደሚከፈል ተጣርቶ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

3.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

የተከፋይ ሂሳብ ልዩነት ተብሎ ለተጠቀሰው ሂሳብ መግለጫው ሪፖርት ድምርና የዝርዝር መነሻ ቀት ድምር ልዩነት ይታያል ተብሎ የተጠቀሰው የሂሳብ መግለጫው ሪፖርት ድምር 53,945,245.34 ሲሆን የዝርዝር በየአካውንት ኮዱ የተቀመጠወም ድምር የገጠመ እና ብር 53,945,245.34 መሆኑን እየገለጽን መረጃውን 17/አስራ ሰባት/ ገጽ በአሁኑ ወቅትአያይዘን አቅርበናል፡፡የተሰጠውንም አስተያየት ተቀብለን ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡

4. <u>የበጀት ሂሣብ፣</u>

4.1 ግኝት፣ <u>ባልታወጀ በጀት እንደ ወጪ ተይዞ የተገኘ፣</u>

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል 1 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 9 "የበጀት ቁጥጥር፡- ማለት በተፈቀደው የበጀት ዝውውር ላይ በማዕከላዊነት ቁጥጥር ለማድረግ እንዲቻል ተገቢውን መረጃ ለማግኘት ወይም ውሳኔ ለመሰጠት እንዲሁም ከበጀት በላይ ወጪ ያለመደረጉን ለመቆጣጠር የሚረዳ የበጀት አመዘጋገብ ስርዓት ነው፡፡" ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚሁ መሰረት መስራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ2009 በጀት ዓመት በሂሳብ መደብ 6116 (ለሰራተኞች የሚደረጉ የተለያዩ ክፍያዎች) ብር 299,280.39 ባልታወጀ በጀት ዝውውር በማድረግ በወጪ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

4.2 <u>ስጋት፣</u>

ባልታወጀና በጀት ማዘዋወር ቀድሞ በዕቅድ ላልተያዘና ላልታለመለት ስራ ወጪ ማውጣት መንግስት ላላስፈልጊ ብድር ሊዳረግ እንዲሁም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

4.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባልታወጀ የሂሳብ መደብ የበጀት ዝውውር ማድረግ አግባብነት የለውም፡፡ ቀድሞ በዚህ የሂሳብ መደብ ክፍያ መከፈሉ አስፈልጊ መሆኑ ከታመነበት እንዲታወጅ ማቅረብ ይገባ ነበር፡፡ የበጀት ዝውውርም ሲደረግ ቀድሞ ከታወጀ በጀት ላይ ብቻ መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

4.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ባልታወጀ በጀት እንደ ወጪ ተይዞ የተገኘ ተብሎ የተገለጸው ለመ/ቤታችን ለበጀት ዓመቱ ከታወጀው ውስጥ ማለትም ከ6100 ፣ 6200፣ 6300፣ 6400 በጀት ውስጥ ላልተያዙ የወጪ መደቦች ከታወጀው በጀት ሳይበልጥ በአንድ ኘሮግራም ሥር ላሉት አዛውሮ መጠቀም የመ/ቤቶች ሥልጣን ሲሆን የበጀት ዝውውር ህጉ የሚያግደው ከካፒታል በጀት ለመደበኛ

በጀት አዛውሮ መጠቀም እና እንደሁም ከደመወዝ በጀት ወደሥራ ማስኬጃ በጀት የሚደረጉ ዝውውሮችን እንጂ ከአንድ ፕሮግራም ወደሌላው ፕሮግራም የሚደረጉ ዝውውሮች በገ/ኢ/ት/ሚ/ር ይሁንታ አግኝተው ዝውውር የሚፈጸም ሲሆን ከአንድ ፕሮግራም ውስጥ የኮድ ዝውውር የመ/ቤቱ ኃላፊነት መሆኑንና ለምዝገባ ገ/ኢ/ት/ሚ/ር እንደሚቀርብ ህጉ ይፈቅዳል ስለዚህ የተፈጸመው ዝውውር ከታወጀ በጀት ላይ መሆኑን እየገለጽን ይህ ግንዛቤ እንዲያዝልን እንጠይቃለን፡፡

4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ "ባልታወጀ በጀት እንደ ወጪ በአንድ ፕሮግራም ሥር ላሉት አዛውሮ መጠቀም የመ/ቤቶች ሥልጣን መሆኑን እና ህጉ ይፈቅዳል፡፡" ቢልም ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ 6116 ለሰራተኞች የሚደረጉ የተለያዩ ክፍያዎች ላይ ቀድሞ ባልተፈቀደ ማዛወር ስለማይቻል የተመለሰው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ ለወደፊቱ የሂሳብ መደቡ አስፈላጊ ከሆነ ቀድሞ በዕቅድ በመያዝ እንዲታወጅ መደረግ አለበት፡፡ በጣም አስፈላጊ ከሆነ እንኳን ተጨማሪ እንዲታወጅ ከሚመለከተው አካል ጋር መነጋገር ያስፈልጋል፡፡ ለወደፊቱ በልታወጀ የሂሳብ መደብ ላይ ማዛወር ስለማይቻል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

5. <u>ንብረት፣</u>

5.1.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>የንብረት አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ፣</u>

የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል2 (ለ) የንብረት አስተዳደር ተግባርን የሚያከናውነውን የሥራ ክፍል የተጠናቀረ መረጃ የያዘ የንብረት መመዝገቢያ ካርድ መዝገብ መያዙን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት የሚለውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ንብረቶች በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው (ፖስታ ቤት፣ አሽዋ ሜዳ፣ አቃቂ፣ ሱልልታ እና ዋና መ/ቤት ጨለቅለቅ ህንፃ) የተቀመጡ በመሆናቸው ለቁጥጥር አስቸጋሪ መሆኑን፣
2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በርመኮን ኢንጅነሪንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ጋር በ30/09/2008 ዓ.ም እስከ 30/01/2008 የሚፀና ውል በብር 5,929,999.15 ተዋውሎ ወደ ተግባር መግባቱ ከሰነዱ የተረጋገጠ ቢሆንም በኦዲቱ ከታዩት መጋዘን ውስጥ፡-

- ፖስታ ቤት ምንም ዕድሳትም ሆነ የንብረት ማስተካከል ያልተደረገ እና ሚ/ር መስሪያ ቤቱ ሲቋቋም የገቡ ንብረቶች እንዳሉ እና በብልሽት ላይ የሚገኙ መሆኑን፣
- ሱልልታ ያሉ ንብረቶች ትልቁ መጋዘን ዕቃዎች በመደርደሪያ የተቀመጡ ሲሆን፣ በጎንና በኃላ በኩል ያሉት ክፍሎች ውስጥ ንብረቶች አቀማመጥ ምቹ ያልሆነ እና መሬት የተቀመጡ ወደ 156 የሚደርሱ አዲስ ወንበሮች ከነ ማሸጊያቸው እየተበላሹ መሆኑን፣
- አሸዋ ሜዳ የሚገኙ ንብረቶች በጣም ብዛት ያላቸውና የተስተካከሉ ቢሆንም መሬት ላይ የሰርቨር ዕቃዎች መኖራቸው፣
- አቃቂ ያሉ ንብረቶች ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ ያሉ መሆናቸው እና ዕድሳትም እንደተጠበቀው አለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

3. የንብረት ክፍል ጠባቂ፣ ተረካቢ፣ አስረካቢ እና ምዝገባ የሚካሄደው አሸዋ ሜዳ፣ አቃቂ፣ ፖስታ ቤትና ሱልልታ አንድ ሰው መሆኑ የስራ ክፍፍል አለመኖሩን፣
4. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወቅቱ የማይጠቀምባቸውን ዕቃዎች በብዛት እንዲገዙ በመደረጉ ያላግባብ እንዲባክን ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ በመግዛት በየንብረት ክፍሉ በብዛት ማከማቸት ትክክለኛ አሰራር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ግድፈቶች የታዩ ለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

5.1.2 ስጋት፣

- በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ዕቃዎች ያለምንም ጥበቃ ማስቀመጡ ንብረቱ ቢበላሽ ለሌላ ተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡
- በአንድ ሰው ብቻ ማሰራቱ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አስቸጋሬ ሊያደርገው ይችላል፡፡
- እንዲወገዱ ተለይተው በታወቁና በሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ሪፖርት የተደረጉ አሮጌ ንብረቶች ላይ ወቅታዊ እርምጃ አለመውሰድ ንብረቶቹ ለበለጠ ብልሽት እንዲዳረጉና ዋጋ ወደ ማጣት ሊደርሱ ይችላል፡፡

5.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንደገለፀው "ፖስታ ቤት ያለው መጋዘን ማለትም ፓፓሲኖስ በተባለ ህንፃ ስር ግራውንድ የሚገኝ ንብረት መሆኑን የንብረት መጋዘን እድሳት ላይ

በፕሮፖዛል አልተጠቀሰም ምክንያቱም ካለው ጥበት አንፃር ለመ/ቤቱ ብዙም አገልግሎት ሊውል የሚችል ባለመሆኑ" ተብሎ ምላሽ ቢሰጥም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከሴፍ የጥበቃ አገልግሎት ድርጅት ጋር "የውል ቁጥር 555/810/08 በቀን 16/12/08 ልደታ ክፍለ ከተማ የቀድሞ ፓፓሲኖስ ህንፃ የሚገኘውን የሚኒስቴሩ መስሪያ ቤት መጋዘን ንብረቱን፣ የሰራተኞቹንና የደንበኞችን ደህንነት ለማስጠበቅ ቅዳሜና እሁድ ጨምሮ 24 ሰዓት አገልግሎት" ለማግኘት የተዋዋለ ሲሆን መ/ቤቱ የሰጠው መልስ እርስ በርሱ የሚጋጭ መሆኑ መመልከት የሚቻል ሲሆን እንደተባለው ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ብዙም አስፈላጊ ካልሆነ በሦስተኛ ወገን ማስጠበቂ ሆነ ቦታውን መያዙ ተገቢ አልነበረም፡፡በወቅቱ ከታየው ጋርም የጠሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፤ስለዚህ የተሰጠው መልስ ትክክል አይደለም፡፡

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሱልልታ ያሉት 156 ወንበሮችን በተመለከተ ንብረቶችም ቀደም ሲል ከፕሮጀክት ስራ የተመለሱ መሆናቸውን ቢገልፅም በአካል የታየው በፕሮጀክት ስራ ወቅት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መጥቶ የተረፈ አዲስ ወንበሮቸች መሆናቸውና ከትልቁና ከተንጣለለ ግቢ ውስጥ ቢሆንም በጆርባ በኩል ካለው መጋዘን ያለ መሆኑ በምልከታ ወቅት የታየ በመሆኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ወደ እርምት መግባት አለበት፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አሸዋ ሜዳ ያሉ ንብረቶች በተመለከተ በየክልሉ የሚደራጁ ወጣቶች እንደተገዛ ቢገለፅም ብዛት ያለው የኮምፒተር በመሆኑ ለረጅም ጊዜ ከቆየ ለብልሽትም ስለሚዳረግ እንደተባለው በፍጥነት ወደ ተግባር በመግባት ንብረቱ ለታለመለት አላማ መዋል አለበት፡፡ እንዲሁም የሰርቨር ዕቃውን በተመለከተ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በወቅቱ የማይጠቀምበትን ንብረት ገዝቶ ማስቀመጥ ያላግባብ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ስለሚዳርግ እና በወቅቱም እንደተባለው መሬት የተቀመጠ በመሆኑ በቂ ጥበቃ በማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አቃቂ ስላሉ ንብረቶች ማስቀመጫ መጋዘን በተመለከተ የዋጋ ፅፅር ቀድሞ እንደተሰራ ቢገልፅማ የተባለው የዋጋ ማነፃፀሪያ ባልቀረበበት የተሰጠው አስተያየት ተቀባይነት የለውም፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ "ስለስቶር ሰራተኛ ጉዳይ ጠባቂ ተረካቢ አስረካቢ ተብሎ በሶስት ሰው ስራ መካሄድ አለበት የተባለው ጠባቂ የተባለው ዘበኞች ተቀጥረው የሚጠብቁ አሉ" ብሎ ምላሽ ቢሰጥም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስለ ንብረት አጠባበቅ፣ንበረት ሲገባ ሲወጣ እና ሲመዘገብ በምን መልክ እንደ ሆነ በወጣው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ጥበቃ ማለት ከውጪ የሚጠብቀውን ጥበቃ አለመሆኑ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል፡፡ ስለዚህ የተሰጠው መልስ አግባብ አይደለም፡፡

- በአጠቃላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለንብረት ማስተካከል ከአንድ ድርጅት ጋር ተዋውሎ ወደ ስራ የገባ በመሆኑ ሁሉም የንብረት ክፍሎች ውስጥ ያሉት ንብረቶች በአንድ ወጥ አሰራር መስተካከል አለበት፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የማስተካከያ እርምጃውን ወስዶ ማሳየት አለበት፡፡

5.1.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፣</u>

ፖስታ ቤት ያለው ንብረት መጋዘን ምንም ዓይነት ዕድሳት ያልተደረገለት መሆኑን እንደጉድለት የተነሳው በቅድሚያ ለግንዛቤ ያህል ለማስቀመጥ ይህ መጋዘን ፓፓሲኖስ በተባለ ህንፃስር ግራውንድ የሚገኝና በጥሩ ይዞታ የሚገኝ ዝናብም ሆነ ፀሃይ እነዲሁም ንብረቶችን ለጉዳ የሚዳርግ ነገር እንደሌለው ንብረቱን በአካል ስናስጎበኝ በግለፃችንንና መታየቱ ይታወሳል፡፡

ይህም ሆኖ በኦዲት ጉብኝቱ ውስጥ የነበሩትን ዕቃዎች ወጥተው ለተፈለገው አገልግሎት እንዲውል ፀድቶና ተዘጋጅቶ እንዲቀመጥ ተደርጓል የንብረት መጋዘን እድሳት ላይ በፕሮፖዛል አልተጠቀሰም ምክንያቱም ካለው ጥበት አንፃር ለመ/ቤቱ ብዙም አገልግሎት ሊውል የሚችል ባለመሆኑ ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩ ምላሽ ለመስጠት፡-

<u>ማስተካከያ አልተደረገለትም የተባለው</u>

1 የሚወገድ ንብረት ነው ይዞ የነበረው ይህም እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡ ሊያገለግሉ የሚችሉ ንብረቶችን በዓይነት ተለይተው ወደ ሌላ ግምጃ ቤት ተወስደዋል፡፡ ለንብረት ተመላሽ እንዲሆን ፀድቆና ተሞልቶ ዝግጁ ሆኖ ይገኛል፡፡

2 <u>ሱሉልታ ያሉ ንብረቶችን በመሬት ላይ የተቀመጡ ወደ 156 የሚደርሱ ወንበሮች ያሉ ንብረቶች ጉዳይ በተመለከተ፡-</u>

ይህ መጋዘን በውስጥ 156 ወንበሮች ብቻ የያዘ ሳይሆን ትልቅና የተንጣለለ ግቢ ሆኖ በመጋዘኑ ውስጥ የተለያዩ ንብረቶች በስርዓት ተቀምጠውና ኮድ ተሰጥቷል፡፡ በጉብኝት በኦዲት ቡድኑ እንደተመለከተ አጠቃላይ ይዘቱም እጅግ በጣም ጥሩ እንደሆነ በወቅቱ በራሳችሁ እንደበት ተገልፃልናል፡፡ 156 ወንበሮች ጉዳይ የቦታ ጥበት በመኖሩ ንብረቱን

በስርዓት ደርድረን ቦታ አዘጋጅተን ለማስቀመጥ ስራው በሂደት ላይ እንዳለ እና እስካሁን የቆየበት ሁኔታም ንብረቶች ገቢ ወጪ ሰነድ እና ዋጋ እየተተከለ ከነሙሉ ታሪካቸው ወደ ሲስተም እየገቡ ስለሆነ እነዚህን ንብረቶችም ቀደም ሲል ከፕሮጀክት ስራ የተመለሱና ሰነዳቸውም ተፈልጎ የማሳታረቅ ስራ እስኪሰራ ድረስ እንደሆነና ይህም ሆኖ ስራው በሂደት ላይ እንዳ መግለፃችን የሚታወስ ነው፡፡ ከአሁን ቀደም ሲል ባለ ሁኔታ ሳይሆን ባያችሁን በሶስተኛው ቀን የማስተካከያ እርምጃ መውሰዳችን ምላሻችንን እናቀርባለን፡፡

3- <u>አሸዋ ሜዳ ያሉ ንብረቶች ብዛት ያላቸው መሆኑ ጉዳይ፡-</u>

በጉብኝት ወቅት ይህ ንብረት በተመለከተ ለምን ይህን ያህል ተከማቸ ብለው ጥያቄ አንስተዋል፡፡ በየክልሉ የሚደራጁ ወጣቶች አሉ ለእነሱ ተጠቃልሎ የሚላክ ነው፡፡ አብዛኛው ንብረት የሚገዛው ከግዥ ማዕቀፍ በመሆኑ ማግኘት ባለመቻላችን አጠቃልለን መላክ አልቻልንም ለስራው የሚያስፈልጉ ንብረቶች ተጠቃልለው ስራው ተግባራዊ አይሆን በሚል ማስረዳታቸውንና ሁሉም የሚገዙ ንብረቶች ተጠቃልለው እንዲላኩ አሁን መላክ እንተጀመረ ገልፀን አስረድተናል፡፡ ምናልባት በቃል ስለሆነ ተረስቶ ሊሆን ስለሚችል ምላሻችንን ይህን በትህትና እየገለፅን ንብረቱን የመስክ ስራ እንደተጀመረ 5 በተያዘለት የግዜ ገደብ እንደሚጠናቀቅ ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

4- <u>*መሬት ላይ ስለተቀመጡ የሰርቨር ዕቃ፡-*</u>

የለንም መሬት ላይ ተቀምጦ ያየነው ሰርቨር ራክ ነው ትልቅ እና ቋሚ ፍሪጅ የሚያህል ሳይዝ እንደነበረውና ከስር እንዳይነዳ መቀመጫ ባለው ተደርጎ የተቀመጠ መሆኑን ነው በጉብኝት ወቅት በጋራ የተመለከትነው፡፡

5- <u>አቃቂ ስላሉ ንብረቶች የሚወገዱ ቢሆን ሳይነዱ ለበርካታ ጊዜያት ያሉ መሆናቸውን እድሳቱም እንደተጠበቀው አለመሆኑን ተመልክተናል ለሚለው ያለን ምላሽ</u>

ስለሚወገዱ ንብረቶች ጉዳይ ጊዜ መውሰድና የንብረት የማስወገድ መብት የግዥ ኤጀንሲ በመሆኑ እንዲወገዱ በዝርዝር አሳውቀናል፡፡ በአሁኑ ዓመት ግን ራሳችን እንድናስወግድ ውክልና የተሰጠን በመሆኑ ግልፅ ጨረታ አውጥተን ለተወዳደሪዎች ሰነድ በመሸጥ ላይ እንገኛለን፡፡

እድሳቱ እንተጠበቀው አይደለም የተባለው በእኛ በኩል ግልፅ ያልሆነ ጥያቄ ነው ይህ ሆኖ ምላሽ ለመስጠት ያህል በአካል በምናስጎበኛችሁ ጊዜ እና በፎቶግራፍም ተመልቶ ማረጋገጥ እነደሚቻለው የፈረሰ እና ውስጡ ለሁለት የተሰነጠቀ በአቧራ የተሞላ፣ ጣሪያው የተገነጠለ፣ ዙሪያውን ያሉ መስኮቶች የተሰባበሩ፣ ኮለኑ በመኪና ተገጭቶ ባላንሱን ስቶ ሊወድቅ ያዘመመ፣ መሰረቱ ተሰንጥቆ የለቀቀ ይዘት እንደነበረው መመልከት ይቻላል፡፡

ይህ ነው ሙሉ ለሙሉ እነዲስተካከል የተደረገው በወጪ እንፃር ማየት ከተፈለገም በሌላ አካል ተጠንቶ ከቀረበው ውጪ በግማሽ ነው እንዲሰራ በእኛ በኩል በቂ ብቻ ሳይሆን ከበቂ በላይ የተሰራ ስራ መሆኑን ነው የምንገልፀው፡፡

6- <u>ስለስቶር ሰራተኛ ጉዳይ ጠባቂ ተረካቢ አስረካቢ ተብሎ በሶስት ሰው ስራ መካሄድ አለበት የተባለው ጠባቂ የተባለው ዘበኞች ተቀጥረው የሚጠብቁ አሉ</u>

አስረካቢ የተባለው በመዋቅር ደረጃ የንብረት አስረካቢ ሰራኛ የሚል መደብ የለንም ተረካቢ የመጋዘን ሰራተኛ ሆኖ የሚሰራ ሰራተኛ ነው ንብረቱን ቆጥሮ የሚረከበው የገቢ ደሰረኝ ሞዴል 19 የሚቆረጥለት ራን በቻለና በተመደበ ንብረት ሰራተኛ ነው፡፡ ይህ ሰራተኛ ሞዴል 19 ሞዴል 22 ስቶክ ካርድ እና ንብረት ገቢና ወጪ እያመሳከረ ይሰራል ምንም እንኳን የሰራተኛ እጥረት ቢኖርብንም ህጉና መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ነው እየተሰራ ያለው እርምት እንዲደረግበት በተነሳው መልኩ ይስተካላል ቢባል እንኳን ጠባቂ ተረካቢ አስረካቢ የሚል በንብረት ክፍል አሰራር ለኛ አዲስ ስለሆነ እና ከአፈፃፀም መመሪያ ጋር ቢቀርብልን በዚሁ መሰረት ማስተካከያውን የምንተገብር መሆኑን በትህትና ምላሻችንን እናቀርባለን፡፡

5.1.5 <u>**የኦዲተሩ አስተያየት፣**</u>

ከላይ የተሰጠው መልስ ትክክል ያልሆነ እና አግባብ የሌለው ስለሆነ የተሰጠው ምላሽ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለዚህ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በማሻሻያ ሀሳብ ላይ የተሰጠውን እንደ መነሻ በመጠቀም የእርምት እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡

5.2.1 <u>**ግኝት፣**</u> <u>**የተሽከርካሪዎች ይዞታ እና የነዳጅ ስርጭትን በተመለከተ፣**</u>

የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል አራት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 የመንግስት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ፣ ቅባት፣ ዘይት አጠቃቀም እና ቁጥጥር በሚለው ስር "ለበላይ ኃላፊዎች እና ለኃላፊዎች ከሚመደቡ

ተሽከርካሪዎች በስተቀር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ መቅረብ እንደሚኖርበት" መመሪያው ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-

- በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተጠቀሙት የነዳጅ መጠንና ከሸፈኑት የኪ/ሜትር ርቀት በየጊዜው ምዝገባ እየተከናወነ ቢሆንም፣ የማቀናነስ (የማስታረቅ) ስራ እንደማይሰራ ተረጋግጧል፣
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ መኪኖች የህይወት ታሪክ ስንመለከት ለአብነት ካየናቸው ውስጥ የመኪና ታርጋ ቁጥር 4-02973፣ 4-12189 የህይወት ታሪክ የሌላቸው መሆኑን ነስራ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

5.2.2 ስጋት፣

- መኪኖች በከተማ ውስጥ እና ከከተማ ውጪ የሚሄዱበትን በኪ.ሜትር ካልተቀመጠ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የወጣውን የነዳጅ እና ተዛማጅ ወጪዎች ታማኝነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡
- የህይወት ታሪክ አለመያዝ መኪኖች ሊወገዱ ሲሉ ትክክለኛ ዋጋቸው ላይታወቅ ይችላል፡፡

5.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለነዳጅና ተዛማጅ ወጪዎች እና ተሽከርካሪዎች አያያዝ፣ አጠቃቀም እና አጠባበቅ ላይ በሚታዩት የአሰራር ግድፈቶች ላይ የስራ አመራሩ ምልከታውን በመነሻነት በመውስድ የማስተካከያ ስራ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት ተሽከርካሪዎች አያያዝና አጠባበቅ ደንብና መመሪያ መሰረት መስራት ይኖርበታል፡፡

5.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ፣

የማስታረቅ ሰራ አለመስራት ግዥ ኤጀንሲ ባስቀመጠው የሪፖርት ሰንጠረዥ የተባለው የማስታረቅ ስራ በጠቅላላ አገልግሎት ቡድን በኩል እየተሰራ በየወሩ ሪፖርት ይደረጋል፡፡

የተወሰኑ መኪናዎች ሙሉ የህይወት ታሪክ የላቸውም ምክንያቱም አንዳንዶቹ በውርስና በስጦታ የተገኙ በመሆናቸው ሰነዳቸውም በሌላ በኩል የሚገኝ በመሆኑ ነገሩ ቀደም ሲል ያለና በቀላሉ ለሟሟላት የተቸገርን በመሆኑ ሲሆን አሁን የሚመለከተውን አካል ጠይቀን የተሟላ ሰነድ እንዲኖራቸው ለማድረግ በጥረት ላይ እንገኛለን፡፡

6. <u>ልዩ ልዩ፣</u>

6.1 <u>ግኝት፣</u> <u>የሰው ሀብት የውስጥ ቁጥጥርን ስንመለከት፣</u>

የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515 አንቀጽ 19 ስለ መቀጠሪያ ደመወዝ አወሳሰን ንኡስ አንቀጽ1-2 ባሉት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከመነሻ ደመወዝ ገባ ብሎ ለመክፈል ለመቅጠር ስለሚችሉበት የሥራ መደቦች፣ የሚከፈልበትን ደረጃ መረጋገጥ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታ በተመለከተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያለውን አደረጃጀት ሲታይ፡-

- ሰራተኛ ቅጥር እርከን ገባ ብሎ መሆኑን የተመለከትን ሲሆን የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳሬክቶሬት ከፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ማሳወቁን እና ፍቃድ ማግኘቱን ማስረጃ እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ብንጠይቅም ሊቀርብ አልቻለም፣
- እንዲሁም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚጠቀምበት የጣት አሻራ ማሽን በትክክል የታለመለትን አገልግሎት የማይሰጥና ሰራተኛው የሚሰጠውንም የጣት አሻራ የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት እንደማይቆጣጠረውና በየጊዜው ሲስተሙን የማስተካከል (Up Date) እንደማይሰራ ይሄውም፡-
    - በዓመት ፍቃድ ላይ ያሉትን ሰራተኞች እንዳሉ የሚያሳይ መሆኑ፡-
    - ቀድሞ ከነበሩበት ዳይሬክቶሬት ወደ ሌላ ዳይሬክቶሬት ሲዘዋወሩ የጣት አሻራው ማሽኑን ቢጠቀሙም እንደሌሉ ቀሪ እንደሚያደርጋቸው ከሰነዱ ለመመልከት ችለናል፡

6.2 <u>ስጋት፣</u>

- ፍትሀዊ የሆነ ውድድር እንዳይኖር ሊያደርግ እና በሠራተኞች መሀከል እኩል የሆነ የስራ አስተዳደር እንዳይኖር እንዲሁም ላልተፈቀደ እርከን ውስን የመንግስት ገንዘብ ያላግባብ እንዲወጣ በር ሊከፍት ይችላል፡፡ እንዱሁም
- የጣት አሻራ ማሽን በትክክል አለመጠቀሙ ያሉትንና የሌሉትን ሰራተኞች መለየት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡

6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በተፈቀደለት መዋቅር መሰረት የሰው ሀይል ከገበያ ማግኘት ካልቻለ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴርን በማስፈቀድ እርከን ገባ ብሎ እና የሰው

ሀይል አስፈቅዶ መቅጠር የሚቻል ሲሆን አሁንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያስፈቀደበት ማስረጃ ተያይዟ ቢባልም ያልተያያዘ ስለሆነ ካለ አሁንም መቅረብ አለበት።

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የጣት አሻራን እንደ ፓይለት መስሪያ ቤት ወስዶ ሌሎችም እንዲጠቀሙ ያደረገ ሲሆን ይህንን ሲስተም ሙሉ ለሙሉ አለመጠቀሙ ስህተት በመሆኑ የሰው ሀብት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ክፍል ራሱ በክፍሉ ያሉት ሰራተኞች ሰልጥነው መቆጣጠር ይኖርባቸዋል፡፡

6.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

እርከን ገባ ብሎ ለመቅጠር በመጀመሪያ በጋዜጣ በወጣ ክፍት የስራ መደብ ላይ ከገበያ ተመዝጋቢ/ተወዳዳሪ ከጠፋ ዳግመኛ ማስታወቂያ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ አሁንም ተመዝጋቢ/ተወዳዳሪ ከጠፋ ቀደም ሲል የወጡት ተደጋጋሚ የስራ መደቦችን በመግለጽ ለፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር እርከን ገባ ብሎ መቅጠር እንዲቻል የማስፈቀድ ጥያቄ ይቀርብና ሲፈቀድ ቅጥሩ ይፈጸማል፡፡ በስራ መደቦች ላይ ተጨማሪ ቁጥር ሲፈለግም በተመሳሳይ ሁኔታ ለሚኒስቴሩ ጥያቄ ቀርቦ ሲፈቀድ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህ አግባብ እርከን ገባ ብሎ የተፈጸመ ቅጥር ሲኖር በፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር የየመ/ቤቱ የቅጥርና የሰው ሃብት መረጃ ቁጥጥር ስለሚደረግበት ይመዘገባል፡፡ የአደረጃጀትና የመዋቅር ወይም የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን የተመለከቱ ስራዎችም ሲከናወኑ የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር ከየተቋማቱ ጋር ስለእያንዳንዱ የስራ መደብ፤የመደብ መታወቂያ ቁጥር፤የየመደቦቹ ደረጃ፤ እርከን ገባ ብሎ መሆን አለመሆኑ እየተናበበ ነው የሚሰራው፡፡ ስለሆነም በዚህ አሰራር መሰረት እርከን ገባ ብለን እንድንቀጥር በትክክል የተፈቀዱ ስለመሆናቸው ማመሳከሪያ እንዲሆን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላከዉን በአባሪነት አቅርበነዋል፡፡

የጣት አሻራ ማሽን (ኤሌክትሮኒክ የሰአት መቆጣጠሪያን) በሚመለከት የታለመለትን አገልግሎት የማይሰጥ፤ የሰው ሃብት ስራ አመራር የማይቆጣጠረውና በየጊዜው ሲስተሙን የማስተካከል ስራ እንደማይሰራ በኦዲት ሪፖርቱ ቀርቧል፡፡ ማሽኑ የታለመለትን አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን ክፍተቶች እንዳሉት ግልጽ ነው፡፡ ምንም እንኳ ሶፍትዌሩ በያንዳንዱ ሃላፊ ኮምፒተር ላይ የተጫነ ቢሆንም በተገቢው ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚያስችል ስልጠና ባለመሰጠቱ በዚህ ረገድ ክፍተት አለ፡፡ በመስክ ስራ፤

በአመትፈቃድ፤ በወሊድ፤ በህመም በመሳሰሉት ምክንያቶች በስራ ላይ የማይኖሩ ሰራተኞችን ሁኔታ ለመመዝገብም ሆነ ከአንዱ ክፍል ወደ ሌላው ክፍል በሚደረግ ምደባና በመሳሰሉ ምክንያቶች ያለዉን መረጃ አያመለክትም፡፡ ያሉትም እንደሌሉ አድርጎ ይመዘግበዋል፡፡ ስለሆነም ሶፍት ዌሩን የማበልጸግ ወይም ሌላ በተደራጀ መልኩ እንዲሰራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሰው ሃብት አስተዳደር ያሉ ማሽኑን የሚከታተሉ ሞያተኞችም የእውቀትና የክህሎት ክፍተት ስላለባቸው ቁጥጥር ለማድረግ አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል፡፡ ስለዚህ በፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር በኩል ለጊዜው የታገደዉን የአደረጃጀት ሁኔታ ሲለቀቅ ራሱን የቻለ ፕሮፌሽናል ሞያተኛ እስኪመደብለት ድረስ የሰው ሃብት አስተዳደር ከሚመለከታቸው ሌሎች ዳይሬክቶሬቶች ጋር በመሆን የአይቲ ሞያተኞች እገዛን መሻቱ የግድ ይላል፡፡ ስለዚህ ክፍተት መኖሩ መጠቆሙ ትክክል ሆኖ ይህንን ክፍተት ለመድፈን ግን የጋራ ጥረት እየተደረገና አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

6.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በማላሹ ላይ "የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር ከየተቋማቱ ጋር ስለእያንዳንዱ የስራ መደብ፤የመደብ መታወቂያ ቁጥር፤የየመደቦቹ ደረጃ፤ እርከን ገባ ብሎ መሆን አለመሆኑ እየተናበበ ነው የሚሰራው፡፡" ቢልም የተጠየቀውና የተመለሰው ምልሽ ግንኙነት የሌለው ቀድሞ በመዋቅሩ መሰረት ሲቀጠር ከገበያ ከጠፋ "የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር በማስፈቀድ ቅጥር መክፈል የሚቻል ሲሆን የተጠየቀውም እሱን ነው እንጂ ዝርዝር የሰው ሀይል መረጃ አይደለም፡፡ ስለዚህ የተሰጠው መልስ አጋባብነት የለውም፡፡ ስለዚህ የተፈቀደበት መረጃ ካለ ማቅረብ ሲሆን ከሌለ በተፈቀደው መዋቅር መሰረት መሰራት ስላለበት የእርምት እርምጃ እንዲወስድ እንላለን፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን የስራ ትብብር እናመሰግናለን!!